# ሳሙኤል ሞሪስ

በላንድሌይ ባልድዊን

እግዚአብሔር በታላቅ ብርሃን የተገናኘው
አፍሪካዊ ወጣት እውነተኛ ታሪክ።

ተርጓሚ ደረጀ በቀለ

ራዕይ አሳታሚ
አዲስ አበባ 1995 ዓ.ም.

# Samuel Morris
## By Lindley Baldwin

The African boy God sent to prepare an American University for its mission to the world.

ከሚለው መጽሐፍ የተተረጎመ

መጀመሪያ እትም 1990

ይህን መጽሐፍ በሙሉም ሆነ በከፊል ያለአሳታሚው ወይም ደራሲው ፈቃድ ማባዛት የተከለከለ ነው

ራዕይ አሳታሚ

የፖ. ሳ. ቁ. 2332

አዲስ አበባ

RP-TR02 - 2M



# መግቢያ

በኢቫንጀሊካል ኮሌጅ ተማሪ በነበርኩበት ጊዜ በተማርኳቸው ትምህርቶች ሳቢያ ብዙ መፃህፍትን አንብቤያለሁ። እነዚህ መፃህፍት ለትምህርተ መለኮት ዕውቀት የሚጠቅሙ ቢሆኑም እንኳ ሕያው የሆነውንና ጥንትም ዛሬም ወደፊትም የሚኖረውን ዘላለማዊ አምላክ እግዚአብሔርን በሚያስደንቅ ሁኔታ የተረዳሁት ሳሙኤል ሞሪስን በማንበቤ ነው።

በየዕለት ኑሯቸው ውስጥ በተግባር ይኑሩበትም አይኑሩበትም ብዙ ሰዎች በእግዚአብሔር ህልውና ያምናሉ። ክርስቲያኖችን ጨምሮ ችግሩ በእግዚአብሔር ማመኑ ላይ አይደለም። በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተገለፀው ሁሉ በሰዎች ሕልውና ውስጥ ሰርፆ መገኘቱና በማንኛውም የህይወታችን ቅፅበት ውስጥ ሕያውና የሚሠራ መሆኑን ስለ እግዚአብሔር ያለን ግንዛቤ ወይም እምነት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው።

አብርሃምን ሙሴንና ኤልያስን ለመሳሰሉ ሰዎች እግዚአብሔር እንደተገለጠላቸው በአዲስ ኪዳንም በታላቅ ብርሀን ቅዱስ ጳውሎስን እንደተገናኘውና እንዳናገረው ከመፅሀፍ ቅዱስ እንረዳለን። አዎን የሳሙኤል ሞሪስን መፅሀፍ ደግሞ ስናነብ ከመፅሀፍ ቅዱስ ውጪ እግዚአብሔር እውነትም የማንኛውንም ሰው አካሄድ የሚመለከት ጣልቃም የሚገባና የሚመራ ለመሆኑ ማስረጃ ከማግኘታችንም በላይ በዚህ በ2ኛው ክፍለ ዘመን እንኳ ለዚህ አፍሪካዊ ወጣት መገለጡ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለሰዎች መገለጡን የበለጠ ያበራልናል።

ይህም ደግሞ፦-

1/ እግዚአብሔርን ለምናውቅ እኛ ከምናስበው ይልቅ የበለጠ ቅርብ እንደሆነ!

2/ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናነባቸው ታላላቅ ነገሮች ያንድ ዘመን ድርጊቶች ብቻ መስለው ለሚታዩን በኛም ዘመን አምላካችን የሚሠራ መሆኑን ያሳየናል።

ተርጓሚው

# ክፍል አንድ

## የደኑ ልዑል የጦር ታጋች

ጨለማዋ ክፍለ ዓለም በመባል ትታወቅ የነበረችው አፍሪካ ለሌላው ዓለም እጅግ ብዙ እብረቅራቂ የከበሩ ማዕድናትን በማቅረብ የታወቀች ናት። ይሁን እንጂ እነዚህ የከበሩ ማዕድናት በመጀመሪያ ተቆፍረው ሲወጡ እያንፀባርቁም ተራ ድንጋይ እንጂ የተለየ ታላቅነት የሚታይባቸው አይደሉም። ሲቆረጡና ሲሰሩ ግን ቀስተደመናማው ውበታቸው ይወጣል።

አፍሪካ እንደዚሁ እንደተለዩ የከበረ እንቁ እጅግ አንፀባራቂ መንፈሳዊ ውበት ያለውን መሪ ለዓለም አበርክታለች። ዕንቁ የፀሀይን ብርሃን ሙሉ ለሙሉ እንደሚያንፀባርቅ ሁሉ ሳሙኤል ሞሪስ «እውነተኛውን መለኮታዊ ብርሃን» ለዓለም ያንፀባረቀ ወጣት ነው። ከሌሎች መሪዎች ይልቅ የማይበገር ያደረገው ይህ ብርሃን በትውልዱ ያገኘው የራሱ አልነበረም።

ይህ ጥቁር ዕንቁ ወደዚህ ውበት እንዲመጣ ሰማያዊ በሆነ እጅ የመቆረጥና የመሰበር ሂደት ውስጥ ማለፍ ነበረበት። ይህ ሰው ይኼነው የሚባል ታላቅ ዕድል ገጥሞት አይደለም ለዚህ ታላቅ ሥራ የበቃው ያው ብሽህ ከሚቆጠሩት በምዕራብ አፍሪካ ደን ውስጥ ከሚኖሩ ወጣቶች አንዱ ነው። በዚሁ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ውስጥ የአይቮሪ ኮስት ተወላጆች የኩሩ ጎሳ ዝርያ ነው።

የቀድሞ ስሙ ካቡ ሲሆን አባቱም የጎሳው አለቃ ነበር። እንደ ሀገሩ ደንብ ካቡ የበኩር ልጅ ስለሆነ ያባቱ ስልጣን ወራሽ መስፍን መሆኑ ነው። ይሁን እንጂ በክብርና በስልጣን ፋንታ እጅግ ለክፉና ከባርነት እንኳ በታች ለሆነ አሳዛኝ ዕድል አልፎ ተሰጥቷል።

በነዚያ ግዛቶች አካባቢ በጦርነት የተሸነፈ የጎሳ መሪ የጦር ካሳ መክፈል ግዴታው ሲሆን እስከ ሚከፍልበት ጊዜ ድረስ ግን የበኩር ልጁን ለሚካሰው ወገን በመያዣነት መስጠት አለበት። ካሳው ተከፍሎ ሲጠናቀቅ መያዣው ይለቀቃል። ክፍያው ከዘገየ መያዣው በየቀኑ እንዲሰቃይ ይደረጋል። ካቡም የገጠመው ዕድል ይኸው ነበር።

ካቡ ገና ልጅ በነበረባቸው ዓመታት አባቱ ካጎራባች ጎሳዎች ጋር ባደረጋቸው ጦርነቶች በተደጋጋሚ ተሸንፍዋል። በነዚያ የሽንፈት ወቅቶች ሁሉ ካቡ ምንም ትንሽ ቢሆን በመያዣነት ባሸናፊዎቹ የጎሳ መሪዎች ዘንድ ታግቷል። ይሁን እንጂ በጣም ልጅ ስለነበረ



የመጀመሪያውን በደንብ አያስታውሰውም። አባትዬውም ፈጥኖ ካሳ ውን በመክፈሉ ቶሎ ሊለቀቅ ችሏል። በሁለተኛው የሽንፈት ጦርነት ግን ዕዳው በየጊዜው ተከፍሎ እስከሚያልቅ ሊተወለኑ ዓመታት ታስሮ ቆይቷል። ካቡ ስለዚህ አለቃቂ የሕይወቱ ዘመን ምንም ሲናገርበት የማይፈልግበት ዘግናኝ ጊዜ ነው።

ከዚህ መከራ ተመልሶ በቤቱ ጥቂት እንደሰነበተ አሁንም የሱ ጎሳ ብዙ ጥፋት ባስከተለ ሌላ ጦርነት ውስጥ በመግባት ተሸነፈ። ያሸነፈ ውም ጨካኝ የጎሳ መሪ የካቡን ወገኖች ለብል አወደመ፣ መንደሮቻ ቸውንም ሁሉ አቃጠለ። የሚከሰው ተሸናፊው ወገን በመሆኑ የካቡ አባት ለላም ፈልጎ ግዴታውን ለመወጣት ቢጥር እንኳን ከተጎዳው ግዛቱ ምንም ዋጋ ያለውና የሚከፈል ነገር ባለመገኘቱ የአስራ አምስት ዓመቱ ካቡ ወዳንገሸገሸውና ነፃ የመውጣት ተስፋ ወደ ሌለበት መከራው እጁ ታስሮ እየተነዳ ተመለሰ።

በሕዝቡ ላይ አስደንጋጭ ሀዘን በመውደቁ ያለምንም ዕረፍትና ቁጠባ የተሰበሰበውን የዝሆን ጥርስና ሌሎች ዋጋ ያላቸውን ቁሳቁሶች በመያዝ አባቱ በክፍያው ዕለት ቀረበ። አሸናፊውም የጎሳ አለቃ ዕቃውን ተቀብሎ እንደመለሰው ዋጋውን ከተመነ በኋላ ግዴታውን የሚያሟላ ክፍያ ባለመሆኑ ታጋቹ እንደማይፈታ አስታወቀ።

የካቡ አባትም ቢሆን ምንም እንኳ ታላቅ ሀዘን ቢሰማውና ተጨማሪው ክፍያ ቢቸግረውም ልጁን ለማትረፍ የቻለውን ሁሉ ከማድረግ አልተቆጠበም ይህንንም ጥረቱን ለማሳካት ሕዝቡ ያላቸውን የመጨረሻ ንብረት መስዋዕት እንዲያደርጉ አወጀ። ለሁለተኛ ጊዜም ልጁን ይዞ በመመለስ ተስፋ ተሞልቶ የተትረፈረፈ ንብረት ይዞ ቀረበ። ስጦታውን አንድ ባንድ ካስቆጠረ በኋላ ገና የማይመጣጠንና ሌላም ብዙ ተጨማሪ ዋጋ መክፈል እንዳለበት ተነገረው። ያን ወቅት የአሸናፊው ጎሳ መሪ ከጦር ሜዳ የሚማርከውንና በካሳ ያገኘውን ምርኮ በጨው፣ በጌጣጌጥና በመጠጥ ከሴራሊዮን ነጋዴዎች ጋር በመለዋወጥ የደራ ገበያ ያገኘበት ጊዜ ነበር። በተለይም ሩም የተባለውን መጠጥ። ሩም እየጣመው በመጣ ቁጥር የሚገበይበት የአገር ውስጥ ንብረት በውጭ ገበያ ዋጋው እርኪ አለመሆኑና ተስ በቀስም እየተሟጠጠበት በመምጣቱ ምንም ዓይነት የካሳ ክፍያ የመጠጥ አቅርቦቱን ሊያረካለት አልቻለም።

በመጠጥ በተመረዘው አለቃ በሚደርስበት የዕለት ተዕለት ግርፋት እድሜ እንደሌለው የተረዳው የካቡ አባት መልከ ቀና የሆነችውን ሴት ልጁን በማስያዝ ወንዱን በጊዜ ለማትረፍ

እንዲለቀቅለት ጠየቀ። «እኔ ከእህቴ ይልቅ ቅጣቱን መቋቋም ስለምችል እሷ ትመለስ» በማለት ካቡ በመቃወሙ ምንም አማራጭ ያጣው አባት ሴት ልጁን ይዞ ወደመጣበት መመለስ ግድ ሆነበት። በዚህ ጊዜ ነበር ይህ አባት የካቡ የመጨረሻ ዕድል ምን እንደሆን በትክክል የተረዳው።

የካቡ አባት ዳግመኛ መምጣት አለመቻሉን ያወቀው የጎሳ መሪ ካቡ በየዕለቱ እንዲገረፍ ትዕዛዝ አስተላለፈ። ከዚህም በላይ ግርፋቱ በየዕለቱ እየከፋና ረዘም ላለ ጊዜ እንዲቀጥል ተደረገ። እሾህና የሚያቃጥል መርዝ በጅራፉ ጫፍ ላይ በመደረጉም እያንዳንዱ ግርፋት ገላውን በመቅደድ በመርዙ አማካይነት እንደ እሳት የሚነድ ቁስል ይፈጥራል። የዚህ ቅጣት ምርኮ የሆነ ሰው መላ ሰውነቱ በእሳት የጋየ የመሰለዋል። በተገረፈ ቁጥር ያይን ምስክር ወዳባቱ ቤት ይላክና በምን ያህል ቅጣት እንደተሰቃየ በዕየለቱ በመግለጥ የባሰ ሰይከተል ቀሪው ዋጋ እንዲከፈል አስጠንቅቆ ይሄዳል።

የካቡ ገላ ለመዳን ፋታ አላገኘም። የጀርባው ሥጋ ተተልትሏል። ብዙ ደም ስለፈሰሰውና የሚጨመርበትም መርዝ ስላደከመው መቆምም ሆነ መቀመጥ አይችልም መከራውን ለማብዛት መስቀለኛ ግንድ ላይ እንደበድንተወጥሮ ያልቆሰለ አካሉ እየተፈለገና እየተገላበጠ መገረፍ ነበረበት።

## ታምራዊ ነፃነት!

የሚቤዣቸው ያጡ ታጋቾች የሚደርስባቸውን የከፋ ፅዋ ሳይጎነጭ በቅርቡ ሞት ነፃ እንደሚያወጣው ተስፋ ያደረገው ካቡ የመጨረሻ ትንፋሹን በናፍቆት መጠባበቅ ጀመረ። በርካታ የካቡ ጎሳ አባላት በዚህ ጨካኝ ሰው ለባርነት ተዳርገዋል። ሌሎችም በመጠጥ በሚናውዙ ማራኪዎቻቸው እንደጨርቅ ሊበጫጨቁ ካቡ ተመልክ ቷል። መውጫ የሌለውና ከሁሉ የከፋው ግን የርሱ ዕጣ ነው። አጋቹ ወገን አባትየው በየጊዜው ያቀረበው ክፍያ ስላላረካው በፍጥነትና በብዛት አናገኛለን ለሚሉት ተጨማሪ ንብረት ማፋጠኛ አድርገው የያዙት ካቡን በተለያየ አሰቃቂ ዘዴዎች ማሰቃየት ነበር። ይሁን እንጂ ያለቀው የካቡ ጎሳ ንብረት ብቻ ሳይሆን የመጨረሻው ቅጣት ተዘጋጀለት። በቁመቱ ልክ ጉድጓድ ተቆፍሮ እስከአንገቱ እንዲቀበርና አፉ ክፍት እንዲሆን ተደርጎ አደገኛ የሆኑ የምድር ወገብ ሞቃታማ አካባቢ ጉንዳኖችን በሚስብ ጣፋጭ ነገር ይለቀለቃል። ውጤቱም በሰልፍ የሚመጡት ጉንዳኖች ሕይወት ያለውን ሥጋ ቀስ በቀስ



በይና ተበይ እየተያዩ በዘግናኝ ሁኔታ መጨረስ ይሆናል። ጉንዳኖቹ በያንዳንዱ አጥንት ላይ የምትገኘውን ሥጋ ከጋጡ በኋላ የሚቀረው ነጭ አፅም ለወደፊት ባለዕዳዎች ማስጠንቀቂያ እንዲሆን በገዳዩ ደጃፍ በእንጨት ላይ እንዲንጠለጠል ይደረጋል።

ሁለመናው የበሰለውና የዛለው ካቡ በመስቀለኛ ግንድ ላይ ተጠርቆ የመጨረሻው ዕድሉን እየጠበቀ ሳለ ድንገተኛ ነገር ሆነ። እንደ መብረቅ አይነት ብርሃን ከሰማይ ሰንጥቆ ወደርሱ መጣ። በዙሪያው ያሉት ሰዎች ሁሉ መቋቋምና ማየት እስከሚያቅታቸው ታላቅ በነበረው ብርሃን ውስጥ «ተነሳና አምልጥ» የሚል የትዕዛዝ ድምፅ ተሰማ። በዚያ የነበሩት ሁሉ ብርሃኑን አይተዋል ድምፁንም ሰምተዋል። ነገር ግን የሚናገረውን አለዩም።

በዚህ ቅጽበት በሳይንስ አለም ሊካድም ሊገለፅም የማይችል ታላቅ ፈውስ ሆነ። ብዙ ደም የፈሰሰው በድብደባ የደከመው በመርዝ የዛለው ለብዙ ጊዜ ያልተመገበውና እንደጠወለገ ቅጠል የተዝለፈለፈው ካቡ «ተነሳ» የሚለው መለኮታዊ ድምፅ በደካማ ጆሮዎቹ ሲገባ አብሮት ታላቅ ብርታትና ፈውስ በሁለመናው በመሰራጨቱ የታሰረባቸውን ገመዶች ከታች እስከ ላይ እንደ ጉድፍ አራግፎ ወደላይ ዘለለ። በድንጋጤ ከከበቡት ጠላቶቹ መሀል እንደ አጋዘን ደኑን እየሰነጠቀ ከአይታቸው ተሰወረ።

ነፃነትና ፈውስ የሰጠው የዚህ ሚስጥራዊ ብርሃን ምንጭ ምንድን ነበር? ይህ ተዓምር ከካቡ እውቀትና ልምምድ ውጪ ነው። ስለዚህ ነገር የሚያውቀውም የሚጠረጥረውም ነገር የለም። ለሁሉም ሁኔታው እንግዳ ነው። ስለ እግዚአብሔር ሰምቶ አያውቅም። እግዚአብሔርም በሰዎች ሁኔታ ውስጥ ጣልቃ ገብቶ ሊረዳ አለየም። እንደ እርሱው በአንድ ዘመን በከፋ ተሸንፈው ለወደቁት ወገኖች ቤዛ ለመሆን ዙፋኑን ትቶ ወደ ምድር ስለመጣው ሰማያዊ መስፍን በእንጨት ላይ ተሰቅሎ ስለተዋረደው ስለተሰደበውና የቀሰ በቀስ አዝጋሚ ሞት ስለሞተው አዳኝ የሚያውቀው ነገር አልነበረም።

ነገር ግን አንድ እንግዳና የማይታይ ኃይል እንዳተረፈው ተገንዝቧል። እስከዚህ ድረስ የተረዳው ነገር አለ። በትክክል እንኳ መቀመጥ የማይችለው ሰው አሁን ማንም ሊደርስበት በማይችል ታላቅ ፍጥነት ይሮጣል። ያመለጠበት ዕለት አርብ ስለነበር ፈፅሞ አይረሳውም። የነፃነቱ ቀን ያለዋል። በሕይወት ዘመኑ ሁሉ አርብን ያለምግብና ውሃ በፆም ሊያከብረው ኖሯል።

# ሩህሩሁ ብርሃን

ካቡ ከሚከታተሉት ፈላጊዎቹ ለመከላከል እስከ ሚጨልም ድረስ በተቦረቦረ ግንድ ወስጥ ተደብቀ። ጨለምለም እንዳለ ካቡ አንድ ነገር ተረዳ። ካንደኛው ሞት ያመለጠው ለሌላ ለከፋ ችግር እንደሆነ መሰለው። በዚያ ማንም ያለ ሌላ እርዳት ለረጅም ጊዜ መቆየት በማይችልበት ደን ውስጥ ብቻውን ነው። ከሁሉ የከፋው ግን ያለጓደኛ ወይም ያለመሣሪያ ብቻውንና ባዶውን መሆን ሳይሆን ያለአቅጣጫና ያለግብ መሆኑ ነበር። እዚህ ቦታ እደርሳለሁ የሚል ተስፋ የለውም። እያንዳንዱ እርምጃው በዙሪያው ባለው ፍርሃትና ተስፋቢስ ፍፃሜ ትዋጥበታለች።

ወደ ጎሳውና ወደ ቤተሰቡ መመለስ አይደፍርም። እንዲህስ ቢያደርግ ያ ጠላት ወገኖቹን ሁሉ በማጥፋት ይበቀለዋል። ለወገኖቹ ራሱን የሰጠው ወጣት አሁንም ለእነርሱ ደህንነት የግል ሞቱን መቀበልን መረጠ በዚህ ሁኔታ ውስጥ በጣም የሚፈራው ማንኛውም ሌላ ጎሳ ቢያየው በሚያገኘው ጉርሻ ለቀድሞ አጋቾቹ አልፎ የመስጠትን አደጋ ነው። በቀን እንኳ ውስጡ በሚጨልምበት በዚያ ደን ውስጥ በፍርሃትና በጨለማ ተውጦ ሳለ አንድ ሌላ ተዓምር ሆነ። ያ ቀድሞ የፈታው ብርሃን አሁንም ዙሪያውን አጥለቀለቀው። አዎ ያ ታላቅና ሩህሩህ ብርሃን ከአንዱ ሞት አድኖ ለሌላ አይሰጥም። ዛሬን አድኖና ረድቶ ለነገ አይሸነፍም። ሰውን መንገድ አስጀምሮ አይረሳም። ከእንግዲህ አንተ በርታ ብሎ አይለይም። የሕይወት ዘመን ሁሉ ባልንጀራና ጓደኛ ነው። እስከዘላለም ይመራል። የምድርን መከራና ፍርሀት ሁሉ ያዘልቃል ወደ ዘላለማዊም ዕረፍትና ሰላም ያደርሳል። ፈፅሞ ሰውን በመሀል አይተውም እንደዚህስ ባይሆን የዚህ ወጣት መፈታት የቁስሎቹ ሁሉ መዳን መበርታቱና መገስገሱ ሁሉ ምን ትርጉም ይኖረው ነበር? ሌላ የሚያቆስለው ከሆነ የመጀመሪያ ቁስሎቹ ለምን ዳኑ ሌላ ሞት የሚጠብቀው ከሆነ ከመጀመሪያው ለምን ተረፈ? እግዚአብሔር ሊያድነን እጃችንን ከያዘን በኋላ ሌላ መከራ የለብንም። ባንድ ዘመን በሌላ ምድረበዳ ነፃ የወጡ ባሮች በዚያ ሩህሩህ ብርሃን መሪነት ተጉዘዋል። ቀንም ሌሊትም እየመራ ብዙ ዓመት አልተለያቸውም በርግጥም ይህ ተቅበዝባዥ የእስራኤል አምላክ ብርሃን ያስፈልገዋል። መርዛማዎቹ ኮብራ እባቦች በየዛፉላይ ይወናጨፋሉ በመሬቱም ላይ እፉኝቶች በብዛት ስለሚገኙ የካቡ መንገድ ቀላል አልነበረም። የሚወናጨፈው ዘንዶ እንደባትሪ የሚያበሩ አይኖቹ በርቀት ማንነቱን ያስታውቁለት ነበር በመኖሪያቸው ውስጥ ማንም እንዳይዘዋወር በንቃት ኮሽታውን ሁሉ ቢያዳምጡም እንኳ ከእነዚህ ሁሉ የከፉት በዚያ ደን ውስጥ የሰው ሥጋ የሚበሉ የሰው ዝርያዎች ናቸው።



ይሁን እንጂ በእነዚህ ሁሉ ወጥመዶችና አደጋዎች ሁሉ መሀል ያ ብርሃን ካቡን መራው። በዚህ ብርሃን እየተመራ መጓዝና ከአደጋ መዳን ብቻ ሳይሆን የሚመገበውን ፍራፍሬና ሥራሥር በመልቀም ዕለታዊ ኑሮውን ማሸነፍ ቻለ። በዚህ ብርሃን በመረዳትና በሚያሳየው አቅጣጫ በመጓዝ አዞዎች የሞሉባቸውን ወንዞችና ሐይቆች ያለችግር አቋራርጦ ቀን ቀን እየተደበቀ ብዙ ሌሊቶች ከተጓዘ በኋላ ካንዲት ከተማ ዳርቻ ባለ ወንዝ ወደሚለማ እርሻ ደረሰ። እስከዚህ ጊዜ ድረስ ምንም ዓይነት ሰው በመንገዱ ላይ አላጋጠመውም።

ሞት ከሞላበት ደን ውስጥ በሰላም ወጥቶ ራሱን በሰላም ያገኘው ካቡ አካባቢውን ወዲያና ወዲህ ቃኘ። የአካባቢውን ተወላጆች መኖሪያ በማይመስሉ ቤቶች የተዋበች መንደር ከዚህ በፊት ከሚያውቃቸው መኖሪያዎች ሁሉ የተለየ ሆነውበታል። ለመጠጋትም በመፍራቱ በርቀት ወደሚመለከተው የኩሩ ጎሳ ቀስ በቀስ ተጠጋ። የመጣው ወደ ባሪያ ጌቶች ሳይሆን ባሪያ ነፃ ወደሚያወጡ ሰዎች ነበር። ያ ሩህሩህ ብርሃን የመራው ወደ ላይቤሪያ ዋና ከተማ ሞኖቪያ ዳርቻ ነው። ይህ እንግዲህ ከታሰረበት ከመፈታቱና በሰላም ከመመራቱ ጋር ሶስተኛው ተዓምር መሆኑ ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን በአንድ ተዓምር ብቻ አይተውም። ባንዱ ላይ ሌላው ካልተጨመረ የቀድሞው ተዓምር ያለፍጻሜ ይቀራል። ከእግዚአብሔር ጋር መጓዝ ማለት በታምራዊ ሕይወት ውስጥ መኖር ነው። ሁልጊዜ አዲስ ነገር የሚታየው በእግዚአብሄር ቤት ብቻ ነው። «ማለዳ ማለዳ አዲስ ነው ታማኝነትህ ብዙ ነው» ‹ሰቆቃ. ኤር. 3:23›

በዚያ ዘመን መላው ላይቤሪያ በጫካ ሕግ የሚተዳደር ሊሆን ካቡ የመጣበት ሞኖሮቪያ ብቻ ነበረች በዘመናዊ ሕግ የምትተዳደረው በዚህ ለፍራ ማንም ደህንነቱን ሊጋፋው አይችልም ከጫካ ወጥቶ ወደዚህ ከተማ የደረሰበትም ቀን ነፃ እንደወጣበት ሁሉ አርብ ነበር።

# አዲስ ስም

ካቡ በመጀመሪያ የተገናኘው የኩሩ ጎሳ ተወላጅ በሚሰራበት የቡና ልማት ውስጥ ተቀጠረ። ኑሮው በሠራተኞች ካምፕ ውስጥ ሆኖ መኝታና የሥራ ልብስ ተሰጠው። በቀን የተወሰነ ቀለብ ይሰፈርለታል።

አዲሱ ጓደኛው ከሚሲዮናዊያኑ ብዙ ነገሮችን ተምሮአል። እነዚህ በዚህ ቦታ የቡና ተክል ሥራ የሚያካሂዱት ሚሲዮናውያን

በሌላ ወገን ደግሞ ወንጌልን ለተወላጆቹ ያስተምራሉ። የካቡ ጎደኛ መሰረታዊ የሆኑ የክርስትና ትምሕርቶችን እየተማረ ነው። ወደ እግዚአብሔር መፀለይ ጀምሯል። እጆቹን ወደ ላይ አንስቶና ተንበርክኮ ባየው ጊዜ ካቡ በመደነቅ «ምን እያደረክ ነው? ሲል ጠየቀው» «ከአምላኬ ጋር እየተነጋገርኩ ነው» «አምላክህ ማን ነው?» ሲል ጠየቀ ካቡ እሱም «አምላኬም አባቴም ነው» ሲል መለሰለት «ስለዚህ አሁን የምትነጋገረው ከአባትህ ጋር ነው ማለት ነው» አለ ካቡ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ መፀለይን «ከአባቴ ጋር ማነጋገር» በማለት ይገልፀዋል። በዚያ የልጅነት እምነቱ ለካቡ ፀሎት ማለት በርግጥም ልጅ ከምድራዊ አባቱ ጋር እንደመወያየት ያህል ቅርበት ያለውና ቀጥተኛ ነበር።

በሚቀጥለው ለንበት ካቡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ተጋበዘ። አንዲት ሴት በአስተርጓሚ ለተሰበሰበው ሕዝብ ንግግር ታደርግ ነበር። ንግግሯም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሰረተ ሆኖ ስለ ሳውል መለወጥ ትነግራቸው ነበር። ከሰማይ ብርሃን እንደመጣና ታምራዊ ድምፅ ከውስጡ ለሳውል እንደተናገረው በቅድም ተከተል ለተሰበሰበው ጉባኤ እየተረከች ሳለ በድንገት ካቡ «እኔ በትክክል ያየሁት ነው፤ ያንን ብርሃን አይቻለሁ። ያዳነኝና ወደዚህ ያመጣኝ ያ ብርሃን ነው» ሲል ጮኸ። ካቡ ለብዙ ጊዜ ያ ብርሃን ምን እንደሆነ ለምን እንደፈወሰውና በዚያ ደን ውስጥ በሰላም እየመራ ወደዚህ እንዳመጣው ሁልጊዜ ይገርመው ነበር። አሁን ግን ለምን እንደሆነ ሚስጥሩ ሊበራለት ጀመረ።

አንድ ነፍስ ስለ እግዚአብሔር ተረድታ ወደ እምነት እስከአልመጣች አትድንም። ነገር ግን የተነጹትንና ራሳቸውን ለመርዳት ፈፀሞ የማይችሉትን እንግዶች ነፍስ የእግዚአብሔር ምሕረት ሊረዳና ሊያተርፍ ይችላል። የእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድ ከሰዎች ማንነት አይነሳም። የእግዚአብሔርን አሠራር መወሰን አይቻልም። በማንኛውም ጊዜ ለማንኛውም ፍጡር ያልተጠበቀ ነገር ሊያደርግ ይችላል። በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ አምስት ከአንድ እስከ ሃያ ባሉት ቁጥሮች ተመሳሳይ ታሪክ እናገኛለን። በጌርጌሴኖን የመቃብር ሥፍራ በጠንካራ እግር ብረትና ሰንሰለት እየታሰረ የሚጠበቅ አንድ ሁልጊዜ ሌሊትና ቀን በመቃብርና በተራራ ሆኖ የሚጮህና ሰውነቱን በድንጋይ የሚቧጭር አንድ ሌጌዎን አጋንንት ያደሩበት ሰው ነበር። ‹አንድ ሌጌዎን በሮም የጦር ሠራዊት የሠው ኃይል ከአራት ሽህ እስከ ስድስት ሽህ ሠራዊት የሚይዝ ክፍለጦር ማለት ሲሆን ይህም ሰው ከአራት ሽህ የማያንሱ አጋንንት ነበሩበት ማለት ነው።›



ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደሚሄድበት ሥፍራ ሁሉ በሽተኛ ዘመድ ያላቸው እየተሽከሙ በማቅረብ እንዲፈውስላቸው ይረዱ ነበር። ይህ ሰው ግን አጋንንት ያደሩበት በመሆኑ ራሱን አያውቅም። ማንነቱ ውስጥ ጎልተው የሚታዩት እነዚሁ ክፉ ኃይላት እንጂ ሰውየው አልነበረም። ዘመዶቹም ያሉት ርቀው አስር ከተማ በሚባለው ግዛት ውስጥ ስለሆኑ ለአገልግሎት ወደዛው እንደተሰማራ በቁጥር ሃያ እናገኛለን። በጌርጌኖን የሚኖሩ ያካባቢው ሰዎችም ይህን ሰው የሚረዱት ሰንሰለት ሲበጥስና ሌላ ሰንሰለት እግር ብረት ሲሰበር ሌላ እግር ብረት በማግባትና እስራቱን በማጥበቅ ብቻ ነው። ታምር የሚሰራውን ኢየሱስን ባዩ ጊዜ ስለመዳን አልጠየቀም። ይልቅስ የሚኖሩበት ኃይላት ስለራሳቸው ተናገሩ። በዚህ ሁኔታ ያለውን እንኳንስ ስለ እግዚአብሔር ስለራሱም ያማያውቀውን ሰው ጌታ ሙሉ ለሙሉ ሲረዳውና ከየሰውነቱ ላይ የእስራት ሰንሰለቶቹን ሲፈታለት እናያለን።

ለካቡም የሆነለት እንዲሁ ነው። እግዚአብሔር ከባዶ ተነስቶ ረዳው። ይህንንም የሚያደርገው ለአላማው ነው። በዚያ ውስጥ የሚከናውነው መልካም ፈቃድ ስላለው ነው።

ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ላለ ያ ብርሃን ሲያጋጥመው ስለስህንነት ገና አያውቅም ነበር። አንድ አማኝ እንዲያስረዳው ግዴታ ነበርና በመለኮታዊ ምሪት ወደ ሐናንያ ደረሰ። ካቡም በዚህ ሁሉ ታምር ውስጥ ቢያልፍም የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ የሚያበራለት ሰው አስፈለገው። እግዚአብሔር ለዚህ ተግባር ያስቀመጠለት ያቺ ባስተርጓሚ ስለጳውሎስ ትሰብክ የነበረችው ሚሲዮናዊት ሴት ነበረች። ወ/ት ኖልስ ትባላለች። አሜሪካዊት ስትሆን በኢንዲያና ቴይለር ዩንቨርሲቲ የተማረች በቅርቡም ለወንጌል ወደ ላይቤሪያ የመጣች የጌታ አገልጋይ ናት። ካቡን ወደ እግዚአብሔር መንግስት የመራችውና በውስጡም ለተቀጣጠለው ታላቅ የእግዚአብሔር ሥራ ምክንያት የሆነች ሴት ናት።

ይህ ወጣት በወ/ት ኖልስ የሚካሄዱ መንፈሳዊ አገልግሎቶች ሁሉ መደበኛ ተካፋይ ሆኖ ከመንፈሳዊ ትምህርት ባሻገር እንግሊዘኛ ቋንቋን መፃፍና ማንበብ አስተማረችው። ቋንቋውን ቀስ በቀስ እየተረዳ ሲመጣ ውብ የሆነውን የኢየሱስን ታሪክ መረዳት ቻለ። በበረት መወለዱን፣ ኃጢአተኞችንና በሽተኞችን እንዴት እንዳገለገለ! በመጨረሻም የሰውን ልጅ ለማዳን ስለተቀበለው የመስዋዕትነት ሞት ፀዋና ስለትንሳኤው በመረዳት ወደአስፈለጊው እውነት መጣ። ሳያውቀው ያዳናውን ይህን የሰው ልጆች ወዳጅ ለመቀበልና የግል ወዳጁ ለማድረግ ጊዜ አልፈጀበትም።

ነገር ግን ካቡ እስከዚህ ድረስ ብቻ በማወቅ ለመርካት አልቻለም። ስለኢየሱስ የበለጠ በሰማ መጠን የበለጠ ስለርሱ ይራባል። የበለጠ ይጠማል። በምታስተምረው ሚሲዮናዊት መንፈሳዊ ሕይወት ስለሢና እንደሷ ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰው ስሌሎች የሚተርፍ መሆንን ይፈልጋል። ለገዛ ወገኖቹ ለኩሩ ጎሳ በቋንቋቸው ወንጌልን መስበክ ይናፍቃል። ወደርሱ ልብ የፈሰሰው የሰላምና የደስታ ጅረት ከርሱ እየመነጨ ምድሩን ሁሉ ቢያጥለቀልቅ ምኞቱ ነው። ወደ ማንነቱ ሲመለከት ግን ይህ ሁሉ ታላቅ ምኞት እንደጭጋግ በንፋስ ይወሰድበታል ራሱን የማይበቃ ሆኖ ያገኘዋል። አሁን ባለበት ሁኔታ ላይ ያለፈው ታሪኩ የግርፋት ስንበር፤ ፍርሃትና ጥላቻ በማንነቱ ወስጥ ሥር ስለሰደደበት ከዚህ ሁሉ ተላቆ እንደዛች አስተማሪው የተፈታና ነፃ ስልጣን ያለው መንፈስ ሊኖረው ያልቻለ ባለፈውም ባሁኑም ሁኔታ ውስጥ የታሰረ ሰው ነው። ወደኋላ ቢመለከት ከሞት የመረረ ታሪክ ወደፊት ቢመለከት ተስፋቢስነት በነዚህ መሀል ያለ ግን ትልቅ ምኞት የበቀለበት ሰው ነው። አዎ ብቸኛና ተስፋቢስ የተጣለና ያልተማረ ካለበት ሁኔታም ተነስቶ ወደፊት የሚያደርገው ምንም ነገር የሌለው። የሚያንቀሳቅሰው ካለበት ሥፍራ ገፍቶ ፈቀቅ የሚያደርገው ሌላ ኃይልና ተዓምር ይፈልጋል። ይህ እስካልሆነ ድረስ በምኞት የሚቃጠል ተራ የቡና ልማት ሠራተኛ ብቻ ሆኖ ይቀራል። ነገር ግን ይህ ወንጌልን ለወገኖቹ የማዳረስ ሀሳብ የራሱ ወይስ እግዚአብሔር በልቡ ያስቀመጠው ራዕይ ይሆን? ውጤቱን የሚወስነው ሀሳቡ የማነው የሚለውን ጥያቄ መመለስ ነው። በብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች ልብ በማንነታቸው ወደፍፃሜ መድረስ የማይችሉ ተራራ የሚያካክሉ ሸክሞች ሊኖሩ ይችላሉ። በልባቸው ያስቀመጠው እግዚአብሔር ከሆነ ሰዎቹ የቱንም ያህል ታናሽ ይሁኑ የእርሱ ሀሳብ በሕይወታቸው ይከናወናል።

እግዚአብሔር በሰዎች ታሪክ ውስጥ ታምር ይሰራል። እርሱ ታምር ባይሰራ ማንም ምንም ታሪክ አይኖረውም። እንኳንስ የበቃ ታሪክና እነሱም ራሳቸው የማይኖሩ ከታሪክ ገፀ ከሀያዋን ምድር የሚጠፉ ብዙዎች ነበሩ። ከእግዚአብሔር የተነሳ ግን እነርሱም ኖረው ታሪክም ሊኖራቸው ችሏል። ከዚህም በላይ በእግዚአብሔር ሰዎች ሕይወት ዋናና ወሳኝ የሆነው ነገር ተጨባጩና የሚታየው የተቆጣጠራቸው ቋሚው ሁኔታ ሳይሆን ከሁኔታዎች ውጪ የሆነው በማንኛውም ጊዜ ውስጥ ሊሰራ የሚችለው የእግዚአብሔር ታምራዊ ተግባር ነው። ካቡ ሌላ ታዓምር ካልመጣለት የርሱ ነገር አበቃ። የእግዚአብሔር ኃይል አልቆ ታሪካችን አያበቃም። ኃይላችን በደከመ ጊዜ ሌላ ታዓምር በርግጥ ይመጣል። ቆመን አንቀርም በሞታችን እንኳ ቢሆን ሌላ ታላቅ ነገር ይደረጋል።



ካቡ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት ተዓምር እንደሚሰራ የሚያውቀው ነገር የለም። በተቤዥው በኢየሱስ ደም ውስጥ ኃይል አለ። መራራውን ቂምንና ጥላቻን ሁሉ የሚያጠራ መንፈስ ቅዱስ በደሙ ኃይል የታጠበውን ሰው ልብ እያጠራ የእግዚአብሄር ሠራተኛ እንዲሆን ያደርገዋል። እንዲህ ካልሆነ ግን ከሥጋ ቅናትና ከራስ ሁኔታ ተነስቶ እግዚአብሔር ላደረገልን መልካም ሥራ ወንፈል መመለስ አይቻልም።

ካቡ ከደህንነት በኋላ ስለሚመጣው ስለዚህ መለኮታዊ ረዳት ገና አያውቅም። ይህ ረዳት ወደሰው ሕይወት ገብቶ ብርታት የሚሰጠው ሰው ድካሙን ተረድቶ ሕይወቱን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ሲያስረክብ ነው። ከዚህ የተነሳ ነው የእውነት መንፈስ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ለተጎዳው ካቡ የመጀመሪያ ዕርዳት ማድረግ የጀመረው «መንፈስ ድካማችንን ያግዛል እንዴት እንድንፀልይ እንደሚገን እናውቅምና ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይናገር መቃተት ይማልድልናል . . . እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለቅዱሳን ይማልዳል» ‹ሮሜ 8 ፥ 26–27›

ይህ የሚቃትት ረዳት በካቡ ሕይወት ሥራውን ጀመረ። ከዚህም የተነሳ በዚህ ወጣት ሕይወት የፀሎት ፍቅር ፈሰሰ። ከመደበኛ ሥራው ወደ ቤቱ ሲመለስ ሌላ መደበኛ የሌሊት ተግባር ያከናውናል።ይህም በፀሎት መጋደል ነበር። ፀሎቱ እንደ ብዙ የፀሎት ሰዎች በፀጥታ ተንበርክኮ ሀሳቡን ለእግዚአብሔር መናገር ሳይሆን ኃይል የተሞላበት የሚታገለው ሰው ያለ ይመስል ሰውነቱ ሁሉ በእንቅስቃሴ የተሞላና ከፍተኛ ድምጽ ያለበት ነው። ይህ ሁኔታው በሠራተኞች ካምፕ ውስጥ የተወደደ አልነበረም። እነዚህ የሥራና የኑሮ ባልደረቦቹ በካቡ ሁኔታና በሚያሰማው ድምፅ ትዕግስታቸው ተሟጠጠ። በዚያ ለመኖር ከፈለገ ፀጥ ብሎ እንዲኖር ካልሆነ ግን ለብቻው የሚኖርበት አካባቢ እንዲፈልግ አስጠነቀቁት።

በካቡ ሕይወት መቀጣጠል የጀመረው እሳት የበለጠ እንዲነድለት የነፍሱ ምኞት በመሆኑ ፀጥታየማይቻልና የማይታሰብ ነው። ስለዚህ በመሸ ጊዜ ወደጫካ ሄዶ መፀለይን መረጠ። አንድ ምሽት እስከ እኩለሌሊት ድረስ በጫካው ውስጥ ሊፀልይ ቆየ። ከብዙ ጊዜ በኋላ ስለዚያች ሌሊት ሲናገር «ደከሞኝና ልቤ ከብዶ የተጠማሁትንም የመንፈስ ቅዱስ መዳሰስ ሳልጠግብ ወደ መኝታዬ ተመለስኩ። ለማረፍም ተጋደምኩ። ድምፄ ሰው እንዳይረብሽ ፀጥ ቢልም ልቤ በፀሎት ጭልጥ ብሎ ሄደ። በድንገት ያለሁበት ክፍል በብርሃን ተሞላ ። ደነገጥኩ የነጋም መሰለኝ። ይሁን እንጂ በዙሪያዬ ያሉት ሁሉ በሰላም ተኝተው ስለሚያንኮራፉ ንጋት አልነበረም። ከዚህም በላይ ክፍሉን የሞላው ተራ የንጋት ብርሃን ሳይሆን ክብር

የተሞላ ሕያው ብርሃን ነበር። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የልቤ ድካምና ሸክም ተወግዶ ውብጣዊ ደስታ ሲፈስብኝና ሲሞላብኝ ይታወቀኝ ነበር። በውነቱም የዶሮ ላባ ያሕል ቀለለኝ። ባዶ እቃን እንደሚሞላ ነገር እየሞላኝ ከመጣው ኃይል የተነሳ መብረር የምችል መስሎ ተሰማኝ። ደስታዬን መቆጣጠር ስላልቻልኩ በካምቡ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ሰው እስከሚነቃ ድረስ ጮኹ። ከዚያ በኋላ ማንም አልተኛም። አንዳንዶቹ ቀውሷል ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ አጋንንት ገብቶበታል ይሉ ነበር። እኔ ግን ልቤን አውቃለሁ። የሰማያዊ አባቴ ልጅ እንደሆንኩና ላንድ እርሱ ላሰበው ነገር እንዳዳነኝ እየተረዳሁ መጥቻለሁ።»

እንግዲህ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነበር የካቡ መንፈሳዊ ሕይወት የሞላውና ለሌሎች ሊፈስ የሚችልበት ደረጃ ላይ የደረሰው። ከዚህ ጊዜ በኋላ ነው ሌሎችንም የማስተባበርና የመምራት ስጦታ ብልጭታ ሲታይበት የጀመረው ስለመንፈስ ቅዱስ የተማረው ነገር የለም። ነገር ግን የተራበ ልጅ ለመብላት እንደሚናፍቅ በሙሉ ነፍሱ እግዚአብሔርን ስለተራበና ስለተጠማ ጌታ ‹በዮሐ. 7፡ 37-38› «ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል» እንዳለው በመጠጣቱ ካልተጠሙ ሰዎች ልምምድ ውጪ በሆነ መጠን የህይወት ውሃ ከሆዱ ፈለቀ። ምንጭን መደበቅ ስለማይቻልም በግልፅ ሲፈስስ ታየበት።

ካቡ ወደ ሜቶደስት ቤተክርስቲያን ተወስዶ ተጠመቀ። ስሙም ሳሙኤል ሞሪስ ተባለ። ስሙን የመረጠችው ወ/ት ኖልስ ናት። ሳሙኤል ሞሪስ እርሷ ለወንጌል አገልግሎት እንድትበቃ የረዳት በኢንድያና የሚኖር የባንክ ሰራተኛ ነው። ካቡ የመጀመሪያው የወንጌል ፍሬዋ ስለሆነ የዚያ ሰው ውለታ በከንቱ እንዳልቀረ በማስታወስ ሳሙኤል ሞሪስ አለችው።

## የመጀመሪያዎቹ የመሪነት ምልክቶች

ሳሙኤልን ከተጠመቀ በኋላ በጠቅላላው በላይቤሪያ ለሁለት ዓመት ያህል ቆየ። የቡና ልማት ሥራውን ትቶ ወደ ዋና ከተማው ሞኖሮቪያ በመሔድ የተለያዩ የጉልበት ሥራዎችን በመሥራት በሚያገኛት ጥቂት ገቢ በደስታ ይኖር ጀመር። ከማንኛውም ነገር የበለጠ ይተጋ የነበረው ስለመንፈሳዊ ነገር ብዙ ለማወቅ ከመሆኑም የተነሳ በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ ሚሲዮናውያን ሁሉ አነጋግሯል። የበለጠ የሚያስተምረውንም ሰው ከመፈለግ አላረፈም። ከሚያገኘው ሚሲዮናዊ ጋር መቆየት ከእርሱም አዳዲስ ነገሮችን መማር



ይፈልጋል። በዚህ ጊዜ ነበር ብዙ በቃሉ የሚያስታውሳቸውን መዝሙሮች የተማረው። ሙሉ ለሙሉ ትርጉማቸውን ባያውቅ እንኳ በጥሩ ሁኔት ይዘምራቸዋል። በአካባቢው ሕዝብ የተመሰከረለት ለጌታ የሚቃጠል ልብ ያለውና የተቀደሰ ሕይወት የሚመራ ስለሆነ ለመታወቅ ጊዜ አልፈጀበትም ብዙም ሳይቆይ ሌላ ወጣት ወደ ጌታ አመጣ። ሁለቱም በሚያስደንቅ ሁኔት ነው የተገናኙት። ይህ ልጅ ቀድሞ በመያዣነት በተያዘበት ቤት የነበረ ባሪያ ሲሆን ለሳሙኤል መከራ የዓይን ምስክር ነው። ታምራዊውን ብርሃን አይቷል። ተነስቶም እንደሚያመልጥ ለካቡ የመጣውን ትዕዛዝ ሰምቶአል።

ከመያዣነት ታጋች ይልቅ ባሪያ በቀላሉ ሊያመልጥ ይችላል። ፍለጋውም አይበረታም። ይህ ባሪያ ወጣት ቀን ቀን በእጳራጭ መንገድ እየተጓዘ ከብዙ ጊዜ በኋላ ወደ ሞኖሮቪያ ደረሰ። የሳሙኤልን ምስክርነት ለማመን ለሚያመነቱ የአይን ምስክር በመሆን ሁለቱ በአንድነት የሚናገሩትን ያልተዛባ ታዓምራዊ ሥራ በሞኖሮቪያ ታላቅ ሊያተጣ ችሏል። ይህም ወጣት ስለ እግዚአብሔር ከተረዳ በኋላ ሔንሪ ኦኔል በመባል ተጠመቀ።

ሰሙኤል በነበረው የሕይወት ምስክርነትና ሰዎችን ለመንፈሳዊ ነገር ማንቀሳቀስ በመቻሉ የተለየ የአመራር ስጦታ እንዳለው እየተገለጠ የመጣው በቀላሉ ሰዎችን ለእግዚአብሔር እንዲታዘዙ የማድረግ ፀጋው ሲሆን ይህም በንግግርና በክርክር ብዛት ሳይሆን በአገልግሎቱ ሁሉ ውስጥ መንፈስ ቅሉስ በመጋበዝና እንዲሰራ በመማለድ ነበር። በዚህ ሰው ሕይወት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ያለዕረፍት የሚሰራ ባልንጀራው ነው። ሳሙኤል የእግዚአብሔርን ስም ጠርቶ በሚቆምበት ቦታ ሁሉ ታላቅ ኃይል ይወርዳል። የሰዎችም ሁሉ ልብ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር ስለሚሆን ጉባኤው እንደአንድ ሰው ያመልካል።

በሞኖርቪያ ቤተክርስቲያን ስለነፍሳት መዳንና ስለመንፈሳዊ መነቃቃት በፀሎት የሚተጉ ስስት ሴቶች ነበሩ። ይሁን እንጂ ለሌሎች ምሳሌነት ያላቸውና ሌሎችንም ወደ ጌታ ለማምጣት የሚችል ለው ብቅ ሊሉ የሚችሉ። ቢሆንም እነዚህ ሴቶች መፀለያቸውን አላቋረጡም። ከእኩለ ሌሊት እበከ እኩለ ቀን አብረው በፀሎት ይቆያሉ። ከእለታት አንድ ምሽት አንድ ወጣት ወዳሉበት ሥፍራ መጣ። ከማንም ጋር አልተነጋገረም። ብቻ በወለሉ ላይ ተደፍቶ ለብዙ ሰዓታት ፀለየ። ሴቶቹም አዲስ ነፍስ የመጣላቸው መስሎአቸው የምሥራቹን ለማብሰር ወደ ውጭ ሮጡ። ሲመለሱም ወደ ሚፀልይበት ወደ መድረኩ ቀርበው ለማየት ቢሞክሩ ወጣቱ ሳሙኤል ሞሪስ እንጂ ሌላ አዲስ ሰው እንዳልሆነ አዩ። የሚፀልየውም ስለራሱ ሳይሆን ስለሌሎች ነበር። ጠንካራ ፀሎት ነበር

የሚፀልየው ብዙም ሳይቆይ በሚቀጥለው ስብሰባ ሃምሳ ወጣቶች ጌታን የግል አዳኛቸው በማድረግ ተቀበሉ።

ቄስ ስሚርል የተባሉት ሚሲዮናዊ የገዛ ሕዝቡን በተሳካ ሁኔታ ማገልገልና መምራት ካስፈለገ ስለዚህ ነገር መማር እንዳለበትና ለዚህም ወደ አሜሪካ ቢሄድ የተሻለ ስለመሆኑ ለሳሙኤል መከሩት። በሀሰቡ የተደሰተው ወጣት አንዲት ሳንቲም እንኳ ባይኖረውም ለመርከብ የሚያስፈልገውን መቶ ዶላር ጌታ እንደሚያዘጋጅለትና እንደሚሰካለት በልቡ እምነት ተለማው። ይሁን እንጂ በመጨረሻ ወደ አሜሪካ ለመሄድ ሲወስን መሄድ ያለበት መጻሕፍትን ከመማር በላይ ለሆን እጅግ ጠቃሚ ጉዳይ ነበር። እሱን ለመሰለው ሰው የሚሲዮናውያኑ አገልግሎት ተራ ሆኖበታል። ከዚህ በለይ ሊያስኬደው አይችልም። ደህንነት በክርስቶስ እንደሚገኝ አስተምረውታል። ነገር ግን ይህ ደህንነት በየቀኑ ሕይወት ያለው ሆኖ እንዲቀጥል ብዙም ያስተማሩት ነገር የለም። የሚቀረው አንድ ደረጃ አለ ያም ሁልጊዜ ከእርሱ ጋር የሚኖረውን አፅናኝ ማወቅ። ይህ መለኮታዊ አፅናኝ ልቡን ሞልቶታል። የርሱ ችግር ልቡን የሞላው ነገር ሚስጥር በአእምሮው አለመኖሩ ነው። ስለመንፈስ ቅዱስ ያሰማችው ሚሲዮናዊ ከዮሐንስ ወንጌል 14ኛውን ምዕራፍ ያነበበችለት ነች። በዚህ ክፍል መድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለተሰበሰቡት ደቀ መዛሙርቱ እርሱ ወደ አብ ከሄደ በኋላ ሊረዳቸውና ሊያፅናናቸው በየቀኑ ከእነሱ ጋር በመሆን ሊደግፋቸው ስለሚመጣው መንፈስ ቅዱስ በማንበብ አስረዳችው ለመጀመሪያ ጊዜ በልቡና በአእምሮው የተገናኘ ለማስረዳት የሚቻል ነገር ያገኘው በዚህ ጊዜ ነው።

መንፈስ ቅዱስ በዚህ ምድር እንዳለና እንደሚሰራ በሰማ ጊዜ ደስታውንና መገረሙን ሊገልፀበት የሚረዳው ቋንቋ አልነበረውም። ያ አስደናቂ ብርሃን የሚመጣና የሚሄድ ሳይሆን ሁልጊዜ ከርሱ ጋር ያለ የማይለየው መሆኑን ተረዳ። ሚሲዮናዊያን በሚገኙበት ሩቅ ስፍራ ሁሉ እየዞረ ስለመንፈስ ቅዱስ ለመማርና ለመነጋገር ብዙ ተጓዘ። የዮሐንስ ወንጌል 14ኛው ምዕራፍ የሳሙኤል ብቸኛ ጥናት ሆነ። በዚህ ርዕስ ላይ የበለጠ እንድታስረዳው ግድ ያላት ሚሲዮናዊት «የማውቀውን ያህል ነገርኩህ ከዚህ በላይ ስለመንፈስ ቅዱስ አልተማርኩም» ስትል ዕውነቱን ነገረችው። «ይህን የምታውቂውን ያስተማረሽ ማን ነው?» ሲል ጠየቃት። «ብዙውን መረዳት ያገኘሁት ከእስቲቪን መሪት ነው» አለች። ስቲቪን መሪት በኢንዲያና አሜሪካ የሚገኙት ጳጳስ የዊሊያም ቴይለር ፀሐፊ የነበሩ ሰው ናቸው።



ከዚያም «አሁን ስቲቨን መሬት የት ይገኛሉ?» በማለት ሳሚ ጥያቄውን አስረዘመ። «በኒውዮርክ» ስትል መለሰችለት ሴትየዋም። ሳሙኤል ሞሪስ በመስገብገብ «ሳንኘው መሄድ አለብኝ» አለ።

ያለ ምንም ቅድመ ዝግጅት መንገዱን ቀጠለ። በቀጥታ ወደ መርከብ ማቆሚያው ወደብ ሮጠ። ወደአሜሪካ ለመሄድ አሽቆለቆለ። ስለሚያስፈልገው መጓጓዣ አእምሮውን አላስጨነቀም። ለእርሱ መንፈስ ቅዱስ ከሁሉም በላይ ነው። መንገዱን ሊያስተካክልለት እንደሚችል እምኗል። ወደብ እንደደረሰ የሚነኝ መርከብ በማየቱ በደስታ ተሞላ። አባቱ ፀሎቱን ሰምቶለታል።

ትንሽ ጀልባ ከጥቂት መርከበኞች ጋር ካፒቴኑን ይዛ ወደ ዳርቻ መጣች። ካፒቴኑ ወደ መሬት ሊወርድ መልኩ ደስ የማይል ጥቁር ልጅ ፊቱ ተደቅኖ «ኒውዮርክ ስቲቨን መሬት ዘንድ እንደምትወስደኝ አባቴ ነግሮኛል» አለው።

ካፒቴኑም አባትህ የታል? ሲል ጠየቀው። «በለማያት» በማለት ሳሚም መለሰ። ካፒቴኑም እየማለ «እብድ መሆን አለበት መርከቤ መንገደኛ አትጭንም» በማለት አመናጭቆት አለፈ።

ሳሙኤል ሙሉ ቀን ጀልባዋ አጠገብ ተገትሮ ዋለ። ወደማታ ካፒቴኑ ወደ መርከቧ ለመሄድ ጀልባዋ ላይ ሲወጣ ኒውዮርክ እንዲወስደው አስተዛዝኖ ለመነው። የመርከቡ አዛዥ ሊመታው ከቃጣ በኋላ ተወውና ወደ መርከቡ ነጎደ። ሳሙኤል ከአባቱ ተለፉ ፍንከች አላለም። በምንም ዓይነት መንገድ ቢሆን መሄዱ ቁርጥ ስለሆን እስከዚያው ድረስ በአሸዋው ላይ ሌሊቱን ሲፀልይ አሳለፈ። በማግስቱ ካፒቴኑ በጀልባው ወደ ዳርቻ መጣ። አብዝቶ ቢለምነውም ፈቃደኛ አልሆነም። ለሁለት ቀንና ሌሊት ያለ እህልና ውሃ ቆየ። የሚወስደው መርከብ ባያገኝም ተስፋ ቆርጦ ካዚያች ባህር ዳርቻ ፈቀቅ አላለም። እንደሚሄድ እግዚአብሔር በእምነት ሞልቶታል። ወደኋላ የሚመለስበት ምንክንያት የለም። የሚወስደው መርከብ እስኪታዘዝ ጠንክሮ መጠበቅ እንዳለበት ያውቃል። እግዚአብሔር የተናገረውን ያውቃል። እስከሚያደርግ ግን ጠንክሮ መጠበቅ ካልተቻለ መሳፈር አይችልም። የምትወስደው መርከብና ሳሚ እኩል ወደብ ላይ ላይደርሱ ይችላሉ ስለዚህ መጠበቅ ያስፈልገዋል። የሁለት ቀን ርሃብና ብርድ ከታላቁ ያውም ስለመንፈስ ቅዱስ ለመማር ከተዘጋጀበት ጉዞ ሊገታው አይችልም። «ያለ እምነት ደስ ማሰኘት አይችልም ወደ እግዚአብሔር የሚደስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና» <ዕብ. 11:6>።

በማግስቱ እሁድ ነበር። መርከበኞችና ካፒቴኑ እንደተለመደው በጀልባቸው ወደ ባህሩ ዳርቻ መጡ። የካፒቴኑ እግር መሬት ከመርገጡ ያ የኩሩ ወጣት ዛሬ እንደምትወስደኝ አባቴ ሌሊት ነግሮኛል» በማለት በፊቱ ተደቀነ።

ካፒቴኑም በጣም በመገረም ተመለከተው። ሁለቱ የመርከቡ ሠራተኞች ባለፈው ምሽት ጥለውት ስለሄዱ የሠራተኛ ችግር አፋጦታል። የኩሩ ጎሳ ብርቱ መርከበኞች መሆናቸውን ያውቃል። «ምን ያህል እንድከፍልህ ትፈልጋለህ?» በማለት ሳሚን ጠየቀው «ኒውዮርክ ለቲቬን መሬት ዘንድ እስከታደርሰኝ በነፃ አገለግላለሁ» አለ ሳሙኤል ስለደሞዙ። ወዲያውኑ ወደ መርከቡ እንዲወስድ በመታዘዙ ሠራተኞቹ አደረሱት።

ሳሙኤል ፈነደቀ። ፍንክች ሳይል በጠበቀበት በተራበባትና በተጠማባት ሥፍራ ፀሎቱ ተመለሰ። አሸዋውን አራግፎ ወደ አሜሪካ ልትሄድ በተዘጋጀችው መርከብ ላይ ወጣ።



# ክፍል ሁለት

## የባሕር ላይ ጉዞና ውጊያው

መንፈስ ቅዱስንና በረከቶቹን ፍለጋ የአትላንቲክን ውቅያኖስ ያቋረጠ ሰው ቢኖር ሳሙኤል ሞሪስ የመጀመሪያው ነው ለማለት ይቻላል። በባሕር ላይ ጉዞው ከግማሽ አመት ያላነስ ጊዜ ፈጅቷል። ወደሳበውም ግብ ለመድረስ በብዙ መከራ ወስጥ በነዚህ የጉዞ ወራት አሳልፍዋል። የካፒቴኑ ንብረት የሆነችው መርከብ በቀጥታ ከመጓዝ ይልቅ በምዕራብ አፍሪካ ወደቦች እየቆመች በአካባቢው የሚገኙ ጠቃሚ ነገሮችን በመግዛትና ለአካባቢው የሚያስፈልጉትን ደግሞ በመሸጥ ከገበያ ገበያ እየተንቀረፈፈች የምትጓዝ ነበረች

ሳሙኤል በመጀመሪያ ወደ መርከቡ በወጣ ቀን ያጋጠመው በወለሉ ላይ የተዘረረ በሽተኛ ወጣት ነበር። የሚረዳው ከግማቱ የተነሳ በጣም ተጎድቷል። መቆምም ሆነ መቀመጥ አይችልም። የካፒቴኑ ልዩ አገልጋይ በመሆን ይሠራ ነበር። ሳሚ እንዳየው በእጠገቡ ተንበርክኮ ፀለየለት። በሽተኛው መለኮታዊ በሆነ ፈውስ ተጻለሰ። ከመቅፀበት ፍፁም ጤነኛ ሆኖ ተነስቶ ተራመደ።

ሳሙኤል እንዲመገብ ካፒቴኑ አላስተላለፈም። ወጥ ቢቀም ቢሆን ለዚህ ጥቁር መስተንግዶ ለማድረግ ፈቃደኛ አልነበረም። ወደባህር ከሮጠባት ከዚያች የሐሙስ ምሽት ጀምሮ ምንም አልተመገበም። ይህን የተረዳውና አሁን ተፈውሶ ጤነኛ የሆነው ወጣት ድርሻውን በማካፈል ለሳሚ ይመግበው ጀምር።

በዚያች ምሽት ካፒቴኑ ወደ መርከቡ ሲመለስ ከዚህ በፊት የባህር ላይ ጉዞ ልምድ እንዳለው ሳሚን ጠየቀው። የመጀመሪያው እንደሆነ ለካፒቴኑ በነገረው ጊዜ ወዲያውኑ ወደ መሬት እንዲመለስ ትዕዛዝ አስተላለፈ። ምክንያቱም ባህር ያልተለማመደ ሰው የባሕር በሽታ የተባለው ሕመም ስለሚያጠቃው በጣም ግዙፍና ያለማቋረጥ የሰዎችን ጉልበት የምትፈልገው መርከብ ሥራ መቋረጥ ስለሌለበት ነው።

ሳሙኤል በማለተዛዘንና በማረጋገጥ እንደማይታመምና ኒውዮርክ እስከሚደርስ ያለመቋረጥ እንደሚሰራለት ቃል ገባለት። በሳሚ ፀሎት የተፈወሰውም ወጣት ቀርቦ «ካፒቴን እባክህ ውሰደው ምን እንዳደረገልኝ ታውቃለህና» በማለት ለመነለት። በዚያ ምሽት መልህቅ ተጠቅልሎ መርከቧ ተንቀሳቀሰች። ያም አፍሪካዊ ወጣት የአሜሪካን ጉዞውን ጀመረ።

ሕይወት በዚህ መርከብ ላይ የጭካኔ ድግግሞሽ ነው ቢባል ሀሰት አይሆንም። የመርከቧ ባለቤት የሆነው ይህ ካፒቴን ጨካኝ ሰው ነው። ሠራተኞቹን ሲያነጋግር ከእያንዳንዱ ቃል ጋር ጡጫ፣ እርግጫ ወይም እርግማን መከተሉ አይቀርም። ከዚያም በላይ ቆንቋና ነጋዴ ነው። ብዙ የሚነግደው ከአረቦች ጋር ሲሆን እነሱ ደግሞ ከርሱ የባሱ አትራፊዎች በመሆናቸው ላለመበለጥ ሁሉም የሞት ሽረት ትግል ማድረጋቸው የተለመደ ነው።

እንዲሁ የመርከቡ ሠራተኞች ከአራቱም ማዕዘን የተለቃቀሙ ዝብርቅርቅ ቀለምና ባህሪ ያላቸው ሲሆኑ ጥቂቱ ሳሚ በመርከቧ ላይ ተመሳሳይ የለውም። የሱ፥ በዚያ መገኘት መርከበኛውን ሁሉ አስቆጣ። እንዴት እንደሚያስወግዱት ይዶልቱበታል። በሆነ ባልሆነው የዱላና የስድብ ውርጅብኝ በዚህ አንድ ነፍስ ላይ ከመርከበኞቹ ይወርድ ጀመር።

ሳሚ የተመደበው በጣም ከፍታ ባለው ምሰሶ ላይ በመሆን የመርከቧን ሸራ ለመወጠር ወይም ለማላላት በሚደርሰው ትዕዛዝ መሠረት ከሚጠባበቅበት ሥፍራ ላይ ነው። እንዳይወድቅ ለውነቱን ከምሰሶው ጋር በተዘጋጀው ማሰሪያ ይጠርቃል። ለለማጁ መርከበኛ በጣም ዘግናኝ ቦታ ነው። ማዕበሉ ወዲያና ወዲህ በሚያላትማት መርከብ ምሰሶ ላይ ተንጠላጥሎ ነው መውጣት ወይም መውረድ ያለበት። በዚያ ላይ ከምሰሶው ጫፍ ሆኖ መርከቧን የሚያያት በርቀት ወደታች ነው። ባሕሩ ሲወናጨፍ ወደታች ማየት በጣም ያስፈራል። ስለሚያዞረው ሊወድቅ ይችላል። በዚያ ላይ ይህን ሁሉ ተቆጣጥሮ መርከቧ የሚደርስባትን የንፋስ ግፊት የሚቋቋመው የርሱ የሸራውን ገመዶች እንደሚገባ መቆጣጠር ነው።

ጉዞ በጀመሩ በሦሥተኛው ምሽት ታላቅ ማዕበል ተነሳ። መርከቧም ከወዲያ ወዲህ ትላተም ጀመር። በዚህ ጊዜ ገመዶቹ ላልተው ሸራው መርገብ ነበረበት። ለዚህ ሁሉ ግን ምንም ጊዜ አልነበረም። ማዕበሉ ድንገተኛ ነበርና። ጭንቱም ቀላል ያለ ስለነበር መርከቧን መግታት ባለመቻሉ የሠራተኞቹ ሁሉ መረባረብ ከንቱ ሆነ በማዕበሉ ፍጥነት ተነዱ። በዚህ ጊዜ ሳሚ ፀለየ። «አባት ሆይ ስለምትጠነቀቅልኝ አልፈራም። እባክህ ወደዚህ ምሰሶ ጫፍ በመውጣት እንዲህ ከመታገል አድነኝ።»

የታሰረበት ምሰሶ ላይቀር በሚረጨው የማዕበል ውሃ በመበሰበሱ ሳሚ ከተንጠለተለበት ቦታ ሆኖ ያንን ጨዋማ የባህር ውሃ ተግቷል። ከዚህም የተነሳ ወዲያው በጣም ታመመ። በመጨረሻ ከታሰበው ተፈትቶ ወደ ወለሉ ላይ ባወረዱት ጊዜ ሞቶ እንደሰነበተና ሆዱ እንደተነፋ በድን ነገር ተጋደመ። ካፒቴኑም ወደርሱ ቀርቦ



አንድ እርግጫ አቀመሰው። አሁንም ወለሉ በማዕበሉ እየተጥለቀለቀ ነው። ሳሚ የሞት ሞቱን እንደታመመ እጆቹን ወደላይ ዘርግቶ ለመንበርከክ ሞከረ። «አባት ሆይ አሜሪካ እስከምደርስ ለዚህ ሰው በየቀኑ እንደማገለግለው ቃል እንደገባሁለት ታውቃለህ። አሁን እንደዚህ ከታመምኩ ልለራለት አልችልምና እባክህ ይህን ሕመም ከኔ ውሰደው» ከማለቱ በርትቶ ተነሳ በእግሮቹ በመቆም ሥራውን ቀጠለ። ከዚያም በኋላ በመርከቧ ላይ በቆየበት ጊዜ ሁሉ ታሞ አያውቅም።

በማግስቱ ሳሚ ወደ መወጠሪያው ግንድ ላይ እየወጣ እያለ ያ የካፒቴኑ አገልጋይ ጓደኛው ወደርሱ ቀርቦ «ሳሚ ትናትና በማዕበሉ ውስጥ ስትንገላታና ትፀልይ እንደነበር ተረድቻለሁ። እኔ ውስጠኛ ክፍሎች ውስጥ መሥራት አልወድም። አንተ ደግሞ እዚያ ላይ ለመሥራት አልሰለጠንክም። ስለዚህ ቦታ እንለዋወጥ» አለው ሳሚም ፀሎቱ በመመለሱ ተደስቶ እሽታውን ገለፀ።

ሳሙኤል ከእግዲህ የካፕቴኑ አገልጋይ ነው። ስለዚህ የዕለት ተግባሩን ለማወቅ ካፒቴኑ ፊት ቀረበ። ሰክሮ የነበረው አለቃው በቦክስ ስለተቀበለው ራሱን ስቶ በወለል ላይ ተዘረጋ። ሳሚ ወደህሊናው ሲመለስ ምንም እንዳልሆነ ያህል በደስታ ሥራውን ቀጠለ። ስካሩ እየበረደለት መጥቶ ሲረጋጋ ስለ ኢየሱስ ያውቅ እንደሆነ ካፒቴኑን ጠየቀው። ጭጋግ የሸፈናቸው የሩቅ ዘመን ትዝታዎች መጡበት። እናቱንና የልጅነት ጊዜውን አስታወሰ። ይህ ጨካኝ መርከበኛ በዝምታ ተዋጠ። ሳሚ ለካፕቴኑ ተንበርክኮ ፀለየለት። ይህም ለካፒቴኑ መለወጥ ጅማሬ ሆነ።

ይሁን እንጂ ለሌላ ሰፋ ላለ መንፈሳዊ ነገር ጊዜ አልነበረም። ከጥቂት ጊዜ በፊት ያለፈው ማዕበል የመርከቧን ውጫዊ አካል ክፉኛ ጎድቶታል። ብዙ መገጣጠሚያዎች በመወላለቃቸው ውሃ እየሰረገ ይገባል። በቅርብ ትንሽ ደሴት በማየታቸው አቁመው ለመጠገን የንፋሱን አቅጣጫ በመከተል ወደዚያው ተጠጉ።

አናጢዎች የጥገና ሥራቸውን ለማከናወን ተሰማሩ። ሌላው ሠራተኛ በሙሉ መርከቧ እንዳትሰምጥ በመምጠጫ መሳሪያዎች ‹ፓምፕ› ያለማቋረጥ ወደ ውስጥ የሚገባውን ውሃ መምጠጥና ወደ ባህር ማፍሰስ ነበረባቸው። ሳሚም ከመምጠጫዎቹ ባንዱ ላይ ተመድቧል። ውሃው ቀንና ሌሊት ያለማቋረጥ ካልተመጠጠ መርከቧ እየተንሳፈፈች የመቆየት እድሏ አነስተኛ ነው። ይህን የመሰለውን ሥራ ገና ሃያ ዓመት ያልሞላው እንደ ሳሚ ያለ ለጋ ወጣት የሚሰራው ሳይሆን ልምድ ላለው ብርቱና ጠንካር ለው እንኳ ከባድ

ነው። ቢሆንም ሳሚ ከብርቱዎች እኩል ይሠራ ነበር። ይፀልያል ይሠራል።

ድካማቸውን ለማሸነፍ ሰውነታቸውን የበለጠ ለማበረታታት ሠራተኞች ሁሉ ሩም የተባለውን መጠጥ ይታደላሉ። ሳሚም ድርሻው ሲሰጠው «በሰማያት ያለው አባቴ ብርታት ይሰጠኛል» በማለት በመርከበኞች ተወዳጅና ኃይለኛ የሆነውን መጠጥ መለሰ። ለሁለት ሳምንት ያህል ከባዱ የጥገናና የውሃ ማለወገድ ሥራ ቀጠለ። የሳሚ ብርታት ተሟጠጠ። ራሱን የሚስትበት ደረጃ ላይ ደረሰ። ነገር ግን በፀሎት መጠን መንፈስ ቅዱስ በሥጋው ውስጥ የሌለ ብርታት እየጨመረለት በረታ። ጥገናውም ተጠናቀቀ።

## አረመኔውን መርከበኛ ማላመድ

ሁሉም ነገር ተስተካክሎ ዳግመኛ የበህሩ ጉዞ ሲጀመር ለመርከበኞቹ ሁሉ አጠቃላይ የደስታ ቀን ነበር። ካፒቴኑም ለዚያ ቀን ብቻ የሚሰራ ትርፍ የሩም ዕደላ እንዲደረግ አዘዘ። በዚህ ከባድ መጠጥ ተሞልተው ተቀጣጠሉ። ወደ ሰዓት በኋላ ገደማ ሁሉም የሚሳተፉበት የርስ በርስ ድብደባ ተጀመረ። ጠቡ የተጀመረው ምንም ትርጉም በሌለው ቀላል በሆነ የዘር ጉዳይ ሲሆን የተጀመረውም ተስድቤአለሁ በማለት ጓደኞቹን ለመግደል ገጀራ በመዘዘው ማሌዥያዊ ግዙፍ መርከበኛ ነው። ሳሚ ለመግደል በተነሳውና በተፈላጊዎቹ መሀል በመግባት በጨዋ ድምፁ «ተው አትግደል! አትግደል! በማለት ይማልድ ጀመር።

ይህ ጠበኛ ሰው ቀደም ሲል ሳሚን እንደሚገድለው ለመርከበኞቹ ተናግሯል። ጥቁር ሰው አይወድም። የያዛት ገጀራ በሌሎች ጉዞዎች የብዙ አፍሪካውያንን ሕይወት ወደ ፍፃሜ አምጥታለች። መግደል ደስታ የሚሰጠው ሰው ነው። ካፒቴኑ ራሱ እንኳ ይፈረዋል።

ሳሚ ሊገላግለው በተጠጋ ጊዜ መሳሪያውን እንጨት እንድሚፈልጥ ወደላይ አንስቶ አነጣጠረ። ምኞቱን ለመፈፀም ጥሩ አጋጣሚ በማግኘቱ ተደሰተ። ነገር ግን ያልተደናገጠው ሳሚ ቀጥ ብሎ ፊቱ በመቆም በትኩረት ዓይኑ ውስጥ ተመለከተው ራሱንም ለመከላከል ባልተንቀሳቀሰው ሳሚ ፊት ገዳዩ ቀስ ብሎ ያነሳቸውን እጆች ወደታች አወረደ። ፊቱንም አዙሮ ወደመኝታው ሄደ። በማሸነፉ ስም የወጣለት ተደባዳቢ ሂሆን እንኳ ዛሬ ግን ከሰው ሁሉ በላይ የሆነ ኃይለኛ ገጥሞታል።



የተነሳውን ብጥብጥ ዘግይቶ የሰማው ካፒቴን የሚያውኩትን ለመግደል በሁለቱም እጆቹ ሽጉጥ ይዞ ብቅ አለ። በድንገት ሁሉም ነገር ፀጥ እንዲል ጣልቃ በገባው ሳሙኤል ሕይወት ውስጥ ያለውን ታላቅ ሚለጥራዊ ኃይል አልተረዳም። ከሰው ዝርያ ውጭ በሆነ ጭካና የሚኖሩ በባህር ላይ ያሸነፉትን ገድለው የሚጥሉ ይህም ለነርሱ ቀላልና ተራ ነገር የሚመስላቸው ሰዎችን የሚገታውን በአፍሪካዊ ልጅ ሕይወት ውስጥ ያደረውን ኃይል ያ ካፒቴን አልተመለከተም። ሽጉጦቹን እያነጣጠረ ሳሙኤል ለመሳው ሠራተኛ ተንበርክኮ ወደሚፀልይበት ታችኛው ክፍል ወረደ። ለመጀመሪያ ጊዜ ከሳሙኤል ጋር በፀሎት ተባበረ። የሰላም መልዕክተኛ ወደዚህ መርከብ በመላኩ አምላክን አመሰገነ። በዚያው ሰዓት ስለኃጢአቱ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት በመናዘዝ ንስሀ ገባ። የውስጥ ለሚቱም ሲታደስ ተሰማው ይህ እንግዲህ በሳሚ የመርከብ ላይ አገልግሎት የመጀመሪያው ፍሬ መሆኑ ነው።

ሳሚ የካፒቴኑን ክፍል ሊያፀዳለት ፈለገ። ብዙ ብርሀን የማይገባበት፣ ጨለምለም ያለ ያውሬ መኖሪያ ዋሻ ይመስላል። ይህ ቦታ ካፒቴኑ ብዙጊዜ ራሱን በመጠጥ በመሳት የሚያሳልፍበት፣ በብዙ ዓመት የሲጋራ ጭስ የጠቆረ በአቧራና በቆሻሻ የተሳበሰ የብቸኝነት ሥፍራው ነው። ሳሚም ይህንን ክፍል በውሃና በሳሙና ጥሩ አድርጎ አጠበው። በግድግዳ ላይ እንኳ የተንጠለጠሉት መላሪያዎች ተወልውለውና አምረው ሥፍራ ሥፍራቸውን ያዙ። ሳሙኤል በዚህም ቦታ የተናገረው አንድ አባባል አለው። «የእግዚአብሔር መንፈስ ቆሻሻ ባለበት ሥፍራ አያድርም» የመርከቧ አዛዥ እጅግ በመደሰቱ አዲሱን ጽ/ቤት ለመርከቡ ሠራተኞች አለጎበኘ።

ቀስ በቀስ ሳሚ የካፒቴኑን ልብ ሙሉ ለሙሉ ማረከ። ቀደም ሲል አሁንም አሁንም በሚፀልየው ሳሚ ይናደድ ነበር። አሁን ግን ባርኔጣውን ከራሱ ላይ በማንሳት ራሱን ዝቅ አድርጎ ከሳሚ ጋር በፀሎት ይተባበራል። በዚህ ሁኔታ ውሎ ሲያድር ለሠራተኞች በራሽን መልክ ያሚያድላቸውን መጠጥ አቆመ። በባህረኞቹም መሀከል ይነሱ የነበሩትና ለማቆም አዳጋች የነበሩት እነዚያ የርስ በርስ ድብድቦች ከሰሙ። በመጠጥ አደላው ምትክ ካፒቴኑ አንድ ነገር ማድረግ ጀምሯል። ያም ነገር ወደመሰብሰቢያው ስፍራ ሁሉንም ለፀሎት መጥራት። በዚያ ጊዜ ሳሚ ጥርት ባለው ታላቅ ድምፁ በላይቢረያ ሳለ በልቡ ያጠራቀማቸውን መዝሙሮች ሲያንቆረቁር የማያደምጠው አልነበረም። ካፒቴኑና ሠራተኞች በዕረፍት ጊዜያቸው በአንድነት በመሰብሰብ ይሰሙታል። መዝሙሮቹ የተለየ ውበት ያላቸው እያንዳንዱን ነፍስ እያረሰረሰ የሚገባ ኃይል

የሚተላለፍባቸው በመርከበኞቹ የሚናፈቁና የማይሰለቹ ነበሩ። ዘማሪው ሳሚ ብቻ ሆኖ አልቀረም። እሱ ሲጀምር ቀስ በቀስ ሌላ ተቀባይ እያገኘ ከድምፅ ወደ ድምፅ፣ ከፊት ወደኋላ፣ ከዳር ወደመሀል እያጥለቀለቀ ጉባኤው ሁሉ በሕይወት ይሞላል። ለእግዚአብሔር ያላትን ጥማት በማቅረብ ነፍስ ሁሉ በየግል ታመልካለች። የእግዚአብሔር ምህረትና ቅርበት የሚጎበኝበት የተለየ ትርዒት ይሆናል።

ዘመኑን በድብድብ ያሳለፈውና ከጉሮሮው መቆረጥ የተነሳ አንገቱ ላይ ትልቅና ቁልቁል የሚወርድ ጠባሳ ያለው ያ ማሌዢያዊ ሰው በድንገት በጠና ታሞ በአልጋ ላይ ዋለ። ቅስሙ እየተሰበረና የመዳን ተስፋው ሁሉ እየተሟጠጠ መጣ። ሳሚ የዚህን ሰው ቋንቋ አያውቀውም። የሚያገናኛቸው ነገር የለም። ስለህመሙ በሰማ ጊዜ ወደተኛበት ቦታ ሄዶ ፀለየለት። ተፈወሰም። ይህ ግዙፍ ጠበኛ ሰው እግዚአብሔርን አያውቅም። የሚኖረውም እንደመሰለውና እንደተሰማው ብቻ ነው። አቅጣጫና ግብ መልካምና ክፉ በርሱ ሕይወት ፈፅሞ አታወቁም። ያ ሁሉ አሁን እግዚአብሔር ወደርሱ በቀረበና በዳሰሰው ጊዜ ተለውጧል። ለጥቂሮች የነበረው ጥላቻ ከመወገዱ የተነሳ ሕይወቱን እንኳ ስለዚህ አፍሪካዊ አሳልፎ ቢሰጥ ፈቃደኛ ነው።

በአጠቃላይ የመርከቡ ሠራተኞች ከተለያየ የዓለም ክፍል የተሰበሰበው የጋራ ባህልና አመለካከት የሌላቸው፣ የተለያየ ቤትና ትዝታ ያላቸው ቢሆኑ አሁን ግን ሁሉም በአንድ ልብ ከሳሙኤል ሞሪስ ጋር ይዘምራሉ የዘር ልዩነት፣ ቋንቋና ያለፈው የየግል እምነት ተረስቷል። የሳሙኤል አምላክ አምላካቸው ሆኗል። ወደነሱ ያመጣው ያ ታላቅ ብርሃን ሁሉ እስከሚያዩት ድረስ በውስጥ እያበራ በአንድ የወንድማማችነት ማሰሪያ አጣምሯቸዋል።

## ታላቅ ውጊያ

መርከቧ በምዕራባዊ የአፍሪካ ዳርቻ ጥግ ጥጉን እንዲሁም በሚያጋጥሟት ደሴቶች ባደረገችው ንግድ ከወትሮው የተለየ እየቀናትና እያተረፈች በአፍሪካ ውጤቶች ጢቅ ብላ ሞላች። ከጥቂት ወደቦች በኋላ ካፒቴኑ በቀጥታ ጉዞዎን ወደ ኒውዮርክ ያቀናል። ከዚያ በኋላ ነው ለሳሚ የደስታ ጉዞ መሆን የሚጀምረው።

መሽትሸት ሲል በርቀት ትልቅ ደሴት ተመለከቱ። በማግስቱም የመርከቡ ባለቤትና አዛዥ ዕቃን በዕቃ በመለዋወጥ ሊገበያይ የሚችልባቸውን ቁሳቁሶች ይዞ ለመውረድ አሰበ። ዕቃውን



በጀልባ ጭኖ ያለወትሮው በርካታ መርከበኞችን አስከትሎ ለመሄድ ተነሳ። አንድ ችግር እንዳለ በልቡ ውስጥ የተቀመጠ ነገር አለ። ሰዎቹንም አስታጥቋል። በማማው ላይ ያለውንም ጠባቂ በጥንቃቄ በባህር መነፀሩ ደሴቷን እየቃኘ በመሬት ላይ የተለየ ነገር ካየ ምልክት እንዲሰጠው አስጠንቅቋል። ጀልባዋ ከአቅሟ በላይ ስለተጫነች ወደ ኋላ የሚገፋትን መጠነኛ ነፋስ በመቋቋም በቀስታ ትጓዛለች። ከመርከቧ እስከ ደሴቷ ያለውን ርቀት እንዳጋመሱ በመመልከቻው ላይ ያለው ጉበኛ ከደሴቷ ላይ በብዙ አቅጣጫ በብዙ ጀልባዎች ወደ ባሕሩ የሚጣደፉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን እንደተመለከተ ካፒቴኑ ወደ መርከቡ እንዲመለስ ምልክት ሰጠው። ካፒቴኑም ወደኋላው ጎዞ ጀመረ። ነገር ግን የሞላችው ጀልባ ባዷቸውን ከሚያባርሯት በመፍጠን ለማምለጥ አልቻለችም። ብዙም ሳይርቁ በየአቅጣጫው ስለተከበቡ መቅዘፋቸውን ትተው መተኮስ ጀመሩ። የደሴቷ ሰዎች ተኩስ ይገጥሙናል ብለው አላሰቡም። ጀልባዋን ለመያዝ ከዚያም ሙሉ ለሙሉ መርከቧን ያለችግር ለመዝረፍ አስፍስፈው ነበር እንጂ የሚቋቋም ኃይል አልጠበቁም። የደሴቷ ነዋሪዎች ጥቁሮች ቢሆኑ የዝርፊያ መሪያቸው ወገኖቹን የካደ ነጭ ነው። ከጥቂት ሳምንት በፊት ባካባቢው ቆማ የነበረችውን ሌላ መርከብ ሙሉለሙሉ ዘርፈዋል። በዚያ ድል ወኔያቸው የተሰበሰበው ዘራፊዎች ያንኑ ታላቅነታቸውን ለመድገም ተስፋ በማድረግ በባህሩ ላይ ፈሰሱ።

ይሁን እንጂ የሳሙኤል ካፒቴን ከነርሱ የባሰ አደገኛ ሰው በመሆኑ የልብ ልብ ተሰምቷቸው ባህሩን የሞሉትን ጠላቶቹን ለማሸበርና ለመበተን ከአጋሮቹ ጋር አንድ ባንድ እያነጣጠሩ ኢላማቸው ውስጥ የገቡትን ሁሉ ወደ ባህር አንጠባጠቧቸው። በዚህ ጊዜ በተፈጠረው መደናገጥ መርከበኞቹ ወደፊት ለመገስገስ ፋታ አገኙ። ወደመርከቧ ስለተጠጉ በዚያ የቀሩት ሠራተኞች በከፈቱት ከፍተኛ ተኩስ ተሸፍነው ካፒቴኑና በጀልባው ላይ ያሉት ሁሉ በሰላም ወደ መርከቧ ወጡ። ጀልባዋን ወደ መርከቧ ላይ ለመጫን ግን ጊዜ አላገኙም። ካፒቴኑንና ሠራተኞቹን ወደ መርከብ በማውጣት ሠራተኞች ተኩስ ስላቆሙ በነጩ ዘራፊ የሚመራ ሌላ ቡድን በአንደኛው የመርከቧ ጫፍ በኩል ወረራቸው። ብዙ የተጫነችው መርከብ የምትጓዘው በቀስታ ነው። መርከብ ላይ የወጡት ሳልወጡት የገመድ መሰላሎች በያቅጣጫው በመላክ በአጭር ጊዜ ዘራፊዎቹ በመርከቧ ላይ በረከቱ። መርከቧ ላይ ለመርገጥ የመጀመሪያ የሆነውና በእንግሊዘኛ የሚናገረው መሪያቸው ከሠራተኞቹ ጋር ካፖቴኑ እጅ እንዲሰጥ በጩኸት ጠየቀ። ይህ ሁሉ ሲሆን የመርከቡ ለራተኞች ለማይቀረው ጦርነት ቦታ ቦታቸውን ይዘዋል። በየምለሰው ላይ እነጣጥረው ከሚተኩሉት አንዱ

የዘራፊዎቹን አለቃ እንደመታ ተንከባሎ ወደ ባህር ወደቀ። አሁንም ለመዝረፍ ባላቸው ተስፋ የቀሩት ተከታዮቹ መርከቧን ለማቆም ወደ መቆጣጠሪያው ገሰገሱ።

የዘራፊዎቹ አለቃ በተመታ ጊዜ ሳሚ ከካፒቴኑ አጠገብ ነበር። ዘራፊዎቹ ወደ መቆጣጠሪያው ሲገሰግሉ ባየ ጊዜ ሳሙኤልን የመርከቧ ውድ ንብረት ወደሚገኝበት የካፒቴኑ ክፍል ገብቶ ቀርቅሮ እንዲጠብቅ አዘዘው። ይህን ያደረገው የሳሙኤልንም ውድ ሕይወት ለመጠበቅ ሲል ነው

መርከበኞቹ ሌሎችም እንዳይወጡ የወጡትም እንዳያመልጡ በየቦታው የተንጠለጠሉትን የገመድ መሰላሎች ሁሉ በጠሱ። ከዚያም በሁሉም አቅጣጫ መርከቧን ወዳለበሷት ዘራፊዎች ፊታቸውን አዞሩ። ሳሚ ውጊያውን አያይም። የሚለማው የጥይት ድምፅና ወዲያውም ዘፍ ብሎ የሚወድቅ የሚያጣጥር ቁስለኛ ጩኸት ነው። የሞት ሽረት ውጊያ ነበር የተካሄደው። እኩለ ቀን ላይ ብዙ ዋጋ ያስከፈለው የለሳም አየር ነፈሰ። መርከቧም ከእንግዲህ ማንም ላያቆማት ጉዞዋን ለመጀመር ተንቀሳቀሰች። ተኩስ ቆመ። ፀጥታም ሰፈነ። የመልህቁ ሰንሰለቶች ሲጠቀለሉ ሳሙኤል የጉዞው መጀምር ገባው። በመርከቧ መቆጣጠሪያ አካባቢ የነበሩትና ያገኙትን ሩም ከመጠን በላይ በመጠጣታቸው በቀላሉ የተያዙት የመጨረሻዎቹ ዘራፊዎችም የተገኙት ወደ ምሽት ላይ ነበር።

ከዚያም ካፒቴኑ ወደ ክፍሉ ሄዶ እንዲከፍትለት ለሳሚ ምልክት ሰጠው። በሩ ሲከፈትለት በሞትና በሕይወት መሀከል የነበረው ካፒቴን እየተንገዳገደ ገባ። ብዙ ደም ለረጅም ጊዜ ስለፈሰሰው ፊፅሞ ተዝለፍልፍዋል። መቆምም መቀመጥም ስላልቻለ ወለሉ ላይ ተዘረረ። ሳሚ ወደ መኝታው ጎተተው ቁስሉን አጠበና በተቻለ መጠን ተጠንቅቆ አሰረለት። ቀጥሎም በአልጋው አጠገብ ተንበርክኮ ለዚህ ለወዳጁ ነፍሱን በፀሎት አፈሰሰ።

ሳሙኤል ሲፀልይለት ካፒቴኑ ተበረታታ። እጁን በቀለታ በልጁ ትከሻ ላይ በማሳረፍ ወደራሱ በመሳብ በቀስታ «ሳሚ! ፀሎትህ መርከቧንና ሰዎቹን አድኗል። ለዎቻችን አንዳንድ ነገር ተዋጉ። ነገር ግን በቁጥር በብዙ እጅ ተበለጥን። አንድ ለአስር ነበርን። ከጠላቶቻችን ጥቂቶቹ ብቻ ጠመንጃ ሲታጠቁ በሙሉ ግን ሰለትና ዱላ ነበራቸው።ንፋሱ ድንገት መጥቶ መርከቧን ከቆመችበት ባያስነሳት ኖሮ እንደጉንዳን በወረሩን ነበር።»

በማግስቱ ጧት ለሞቱት መርከበኞች ታላቅ ሀዘን ሆነ። ከሠራተኞቹ ብዙዎቹ ቆሰለዋል። ወለሉ በደም ተዘፍቋል። የሚወዳቸው ሰዎች ሬሳ ወደ ባሕር ሲወርድ በመመልከቱ ሳሚ ከባድ



ሀዘን ወደቀበት። በሀዘኑ ለመቆየት ብዙም ጊዜ አላገኘም። ወዲያውኑ ሥራ በዛበት። ለቁሚዎቹ ሀኪምና አስታማሚ በቀረውም ጉዞ ሁሉ አፅናኝ ሆነ። ርኅራሄውና በእግዚአብሔር እርዳታ የመተማመን ልምዱ በመርከቡ ላይ የወደቀውን የሀዘን መንፈስ ለወጠው። ሁሉም ተፅናና። እያንዳንዱ ያለግልምጫና ስድብ ወደየራሱ ተግባር በፈቃደኝነት በመሰማራቱ በጥቂትም ሠራተኞች ቢሆን ቀሪው ጉዞ ሠመረ።

## ኒውዮርክ ሳሚን ተቀበለችው

ከወራት ጉዞ በኋላ ያች የጭነት መርከብ ኒውዮርክ ደረለች። ሳሚ ከመርከብ ሲወርድ በላዩ ላይ ከከረሙት አሮጌ የባሕረኛ ቡትቶዎች ሌላ ወደ ከተማ ሲገባ የሚለብሰው አልነበረም። ያገለገለውም ለጉዞው ስለሆን ገንዘብ የለውም። ስለዚህ መርከበኞቹ ልብስና ጫማ አዋጥተው በልክ በልኩ እንዲሆን ሰፋፍተው አስተካከሉለት። ሳሚ ገና በርቀት የኒወዮርክን ወደብ ሲያይ ሁለመናውን ደስታ ወረረው። ያሳለፋቸው ችግርና መከራ ሁሉ ተረሱት። እየቆየ በመጣ መጠን በመርከቡ ውስጥ ያሉት ሁሉ ወዳጆቹ ሆነዋል። ያ አንድ ዘመን ጠብ ያነፈንፍ የነበረው ማሌዥያዊ ከሁሉ የበለጠ የልብ ወዳጁ ነው። ታላቁንና ተወዳጁን ሰው ሳሙኤል ሞሪስን ለመሰናበት ከበቡት። በየተራ እየጨበጡት ሲሰናበቱት እንደልጅ ያለቅሱ ነበር። የዘር ልዩነት ፈርሷል። ከመወሰድ ባሻገር በአንድ ያስተሳሰራቸው የተለየ ዝምድና እንዳለና እያንዳንዱ የገዛ ወገኑን እንደተለየ ያህል ይሰማው ነበር። እግዚአብሔር በመሀከላቸው ቆዳው የጠቆረ አምባሳደር በማስቀመጡና በርሱም በኩል ልመናን የሚሰማ የግልና በሰዎች መሀከል ልዩነት የማያደርግ አምላክ እንዳለ ተረድተዋል።

መርከቧ ወደ ወደቡ ተጠግታ መረማመጃው እንደተዘረጋ የመጀመሪያው ወራጅ ሰሙኤል ሞረስ መሆን እንዳሰበት ግልፅ ነው። እግሩ መሬት እንደረገጠ በመጀመሪያ ያገኘውን ሰው አስቁሞ «ሊባክህን እስቲቨን መሪትን የት አገኛለሁ?» ሲል ጠየቀው። መንገደኛውም የስቲቨን መሪትን አገልግሎት የተካፈለ በመሆኑ «አውቀዋለሁ በስምንተኛው ጎዳና በከተማው የወዲያኛው ክፍል ይኖራል። አንድ ዶላር ከሰጠኸኝ አደርስሀለሁ።»

መርከቧ የቆመችው ስቲቨን መሪት ከሚታወቅበት አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ሲሆን መንፈስ ቅዱስ ያንን ሰው ወደ ወደብ አምጥቶ ባይገናኙ ኖሮ ሳሚ የሚፈልገውን ሰው ለማግኘት ባልቻለም ነበር። ከኒውዮርክ ከተማ ነዋሪዎች ውስጥ በስም ብቻ የሚያውቀውን ሰው ያለ እግዚአብሔር ምሪት እንዴት ማግኘት ይችል ነበር? አዎ

በዚህ ልጅ ሕይወት እግዚአብሔር ባይኖር በስም እንኳ ብዙ የሚመሳሰሉ ሰዎች ከተማውን ሊሞሉት ይችላሉ። ሳሚ ለስሙ ማስጠሪያ አንዲት ሳንቲም እንኳ የለውም። ቢሆንም ዶላሩ ከሚመጣበት ይመጣልና ሰውየውን ለመሪነት ያዘጋጀ አምላክ ለክፍያው አይሸነፍምና ሳሚ በዋጋው ተስመምቶ መንገዱን ቀጠለ። መሪው በርካታ መንገዶችን እያቋራረጠ በችኮላ በሚራመዱ ሰዎች ወስጥ አያሹለከለከ ስቲቨን መሪት ቢሮ አደረሰው። ዘጋግቶ ለመሄድ የውጭውን በር እየቆለፈ ያለውን ሰው የሳሚ መሪ «ስቲቨን መሪት የሚባለው ሰው ያውልህ» ሲል በጣቱ ወደሰውየው አመለከተው።

ሳሚ ወደ ስቲቨን መሪት እየሮጠ «እኔ ሳሙኤል ሞሪስ ነኝ ከአንተ ጋር ስለመንፈስ ቅዱስ ለመነጋገር ከአፍሪካ ነው የመጣሁት»

ሚስተር መሪት በዚህ ባልተለመደ ሁኔታና ሰላምታ በመገረምና ግራ በመጋባት የተሰጠው መሸኛ ወረቀት እንዳለው ጠየቀው።

ሳሙኤልም «የምጠብቅበት ጊዜ ፈፅሞ ስላልነበረኝ ምንም መሸኛ ደብዳቤ አልያዝኩም»። በማለት መለሰ።

ስቲቨን መሪትም በዚያች ሰዓት ቀጠሮ ስላለውና ሊያነጋግርበት የሚበቃ ሰዓት ስለሌለው ቢጠብቀው ሲመለስ እንደሚወያዩና ለሌሊትም ማረፊያ እንደሚያዘጋጅለትና እስከዛሬም በሚቀጥለው የሚሸኖች ግቢ ውስጥ ሊጠብቀው እንደሚችል በትሕትና ገለፀለት።

ሳሚ ወደሚሽኑ ግቢ እያመራ ሳለ ያመጣው ሰውየ «ገንዘቤ የታል?» ሲል ተጣራ እግዚአብሔር እንደሚያዘጋጅለት ቅንጣት ታሕል ጥርጣሬ የሌለው ወጣት በእጁ ወደ ስቲቨን መሪት እያመለከተ «እሱ ይከፍልሀል» አለው። መሪትም በፈገግታ የሚገባውን ለሰውየው ከሰጠ በኋላ ወደ ሰረገላው ገብቶ ሄደ።

ስቲቨን መሪት ጉዳዩን እንደጨረሰ ወደ ቤቱ ገሠገሠ። ከሰረገላው ሲወርድ ያ የሚጠብቀው አፍሪካዊ ልጅ ትዝ አለው። ተመልሶ ቤቴል ወደተባለው የሚሽን ማዕከሉ እንዲወስደው ለነጂው ነገረው። ሲደርሱም ሳሙኤል በአስራ ሰባት ሰዎች ተከቦ አገኘው ስለኢየሱስ አዳኝነት ነግሯቸው እግዚአብሔር በላደረገላቸው ምህረት በደስታ እየፈነደቁ ነበር። እነዚህ እንግዲህ ሳሚ አሜሪካንን በረገጠበት የመጀመሪያ ምሽት ወደ ጌታ ያመጣቸው መሆናቸው ነው። ስብሰባው ሲበተን መሪት በልጁ ሁኔታ በመገረም ወደ ቤቱ ወሰደው። በዚህ ዓይነት ሰረገላ ሲቀመጥ የመጀመሪያው ነው። እርስ በእርሳቸው እየተጠባበቁ እንደውሃ የሚፈሱት ሰረገላውን የሚስቡት



ፈረሶች የተመልካችን ዓይን ይስባሉ። ስቲቨን መሪት በሀብት የበለፀገ ቤተ መንግስት በሚመስል ቪላ ውስጥ በድሎት የሚኖር ሰውነው። ወደ ቤቱ በመምጫ ሰዓቱ እንደተለመደው ያች የታመነች ሚስቱ ትጠባበቀዋለች። የሰረከላውንም በር ሲከፈት ያንን ጥቁር ልጅ በጨለማው ውስጥ የበለጠ ጨልሞ በማየቷ በድንጋጤ «ለምን? ምንድን ነው ያመጣኸው ስቲቨን?» ስትል ጠየቀች። «አዎን ዶሊ ይኸ ጥቁር መልዓክ ነው» ቢላትም ሲገባትና ልትቀበለው ያልቻለችው ባለቤቱ «ምን ሲያደርግልህ አመጣኸው» በማለት በፊቱ ቆመች። «በጳጳሱ ማረፊያ ክፍል ላሳርፈው ነው» ሲል መለሰላት። «እንዴ በፍፁም አይሆንም» በማለት ተቃወመች። ቢሆንም እንዳለው አደረገ። ዊሊያም ቴለር ወደ ኒውዮርክ ሲመጡ ወደሚያርፉበት ልዩ ወደሆነው ክፍል ይዞት ፎቁን ወጣ። ስለመኝታው ሁኔታ፣ መብራቱን እንዴት እንደሚያበራና እንደሚያጠፋ ካሳየው በኋላ በዚያ ያርፉ ስለነበሩት እንግዳ መጠቀሚያ ከተቀመጠው የሌሊት ልብስ አንዱን አውጥቶ ለሳሚ አለበሰው። ቴለር በጣም ግዙፍ ሰው በመሆናቸው የርሳቸውን ፒጃማ የለበሰውን ሳሚን የተመለከተው መሪት ሳቅ በሳቅ ሆነ።

ነገር ግን ከሳቁ ቀጥሎ በመጣው ጥልቅ ስሜት ወዲያውኑ ተለወጠ። ሳሚ ረጅሞቹን የፒጃማ እጅጌዎች ከጠቀለለ በኋላ እጆቹን ወዳስተናጋጁ በመዘርጋት ለፀሎት አብሮት እንዲንበረከክ ጠየቀው። የሳሙኤል ሞሪስ ነፍስ በመንፈስ ቅዱስ እሳት መቀጣጠል ጀምራለች። እየመራ ያመጣውን ብርሃን አለኝ በሚለውን ታላቅ ነገር ከሚያስተናግደው ከዚህ ሰው ጋር በዚህ ምሽት ሊካፈለው ነው። ይህ ለዓመታት ወንጌልን ለሌሎች ሲሰብክ የኖረ አገልጋይ ከልምምዱ ውጭ በሆነ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተጎበኘ። በነዚያ ጥቂት የፀሎት ደቂቃዎች ፊደል ባልቆጠረው ኒግሮ አማካኝነት የትላቁ መንፈሳዊ ሰው የቴይለርዋና ፀሐፊ የአፀናኙን እውነተኛ ኃይል ተቀበለ።

በማግስቱ ሳሚ ከመኝታው እንደተነሳ አልጋውን በፍጥነት አነጠፈ። ክፍሉን አስተካከለ። ከዚያም ወደ ፈረሶቹ ጋጣ አመራ። በዚያ ጧት ስቲቨን መሪት ዘግይቶ ነበር የተነሳው። «የጥቁሩን መልአክ» አስተዳደር ለማወቅ ወደ እንግዳው መኝታ ቤት ቢሄድም ያገኘው በክፍሉ ውስጥ ሳይሆን የፈረሶቹን ጋጣ የሚያፀዳውን ሰው ሲረዳ ነበር። ስቲቨን መሪት ወደ ቤት ይዞት በመግባት አንድ ባንድ ከቤተሰቡ ሁሉ ጋር ካስተዋወቀው በኋላ ለቁርስ ባንድነት ተቀመጡ።

ስቲቨን መሪትና ቤተሰቡ ከጥቁር ጋር ለምግብ ሲታደም የመጀመሪያ ጊዜው ነው። ይህ እንዴት ሲሆን እንደቻለ ለነርሱ ሚስጥር ነው። በአንፃሩ ለሳሚም ከነጭ ጋር ሲጋበዝ። መሪት አዲሱን ምግብ እንዴት እንደሚመገብ ለሳሙኤል በትሕትና ካሳየው

በኋላ ከህሙስ እስከ ቅዳሜ ጠዋት ያልተመገበው ወጣት እስከ ሚጠግብ ተመገበ።

## ወደ መንፈሳዊ መነቃቃት የተለወጠው የቀብር ስርዓት

ስቲቨን መሪት ሥራ የሚበዛበት ሰው ነው። ጊዜው በሙሉ በቤተክርስቲያን ሥራ የተያዘ ነው። በዚህ ቅዳሜ ጠዋት እንኳ የአንድ የታወቀ ሰው የቀብር ስርዓት ለማስፈፀም መሄድ ነበረበት። በስረገላው ሳሚን ይዞ ወደዚያው አመራ። በመንገዱ ላይም በስርአቱ ላይ የሚረዱትን ሁለት በስነመለኮት የዶተርነት ማዕረግ ያላቸውን የተከበሩት ሰዎች ለመያዝ አቆመ። ከሁለቱ አንዱ ወደስረገላው ለመግባት ሲመለከት ያን ጥቁር ልጅ ለላየው ወደኋላው አፈገፈገ። ምንአልባት ይህ ጥቁር ሻጋታ ልጅ ፈጥኖ በመውረድ ቦታውን ይሰቃል በማለት ጥቂት ጠበቀ። እንደማይወርድ ሲረዱ ሁለቱም ገቡ። ከዚህ አፍሪካዊ ጋር እንዲሄዱ መደረጉ አስገርሟቸዋል። ያለ ንግግር ጥላቻቸውን በፊታቸው ለሳሚ በመግለፅ ጉዟቸውን ቀጠሉ። በሁኔታው የተደናገጠው ስቲቨን መሪት እንግዳው ልጅ እንዳይሰማው የነፈሰውን የጥላቻ አየር ለመለወጥ ይሚያልቁባቸውን ጎዳናና አደባባዮች ሕንፃዎችና መሥሪያ ቤቶች ስም በማስተዋወቅ የሚያስፈልገውንም የማያስፈልገውን ከመናገር አላቆመም። ነገር ግን ሳሚ ከኒውዮርክ አስደናቂ ነገሮች ሁሉ በላይ የሚኀኀለት በልቡ የሞላ ፍለጋና ጥይቁ ስላላ እጁን በመሪት ጉልበቶች ላይ በማድረግ «በስረገላ እየሄድክ ፀልየህ ታውቃለህ?» ሲል ጠየቀው እሱም በእርግጥ ብዙ ጊዜ በስረገላ ላይ በመንፈስ እየተባረከ ተጉዞ እንደሚያውቅ እንጅ መደበኛ ፀሎት እንዳልሞከረ ነገርው። «አሁን እንፀልያለን»። አለው ሳሚ። ተንበርክከው መፀለይ ጀመሩ። ሳሚም በመቀጠል «አባት ሆይ እኔ እዚህ ከመጣሁ ስንብቻለሁ እኔ ላናግረው የምፈልገው ስለመንፈስ ቅዱስ ነው። እሱ የሚነግረኝ ለስኒውዮርክ ከተማ መንገዶችና ሕንፃዎች ነው። እባክህ ካንተ በቀር ለሰሌላ ነገር እንዳያስብ፣ እንዳይናገር፣ እንዳይሰብክና እንዳይፀልይ በህልውናህ ሙላው» ብሎ እንደፀለየ በዚያ ሠረገላ ባሉት ሁሉ ላይ ታላቅ ሀይል ወረደ።

ስቲቨን ሞሪት በአገልጋዮች ምርቃት፣ በታላላቅ መንፈላዊ ጉባኤዎችም ላይ ተከፍሏል ቅዱሳንንም ለሌሎች መነቃቃት እንዲሆኑ እጅ በመጫን አገልግሎት እንዲካፈሉ አድርጓል እሱም ብዙ ጊዜ ተካፍሏል። ነገር ግን በዚህ ሰረገላ ውስጥ የተቀበለው የመንፈስ



ቅዱስ እሳት አይነት ገጥሞት አያውቅም። የመሪት መላ ሕይወት የተለወጠው በዚህች ወቅት ነው።

ከኔግሮ ጋር አብረው መኃዝ ቀደም ሲል ያሳፈራቸው አነዚያ ሁለት ሊቃውንት ክሳሚ የፀሎት አገልግሎት በኋላ በአንፃሩ የራሳቸውን የሻገተ መንፈሳዊ ሕይወት አሳፈራቸው። ምንም እንኳ ውጫዊው ሁኔታው የተጎሳቆለ ቢሆንም ውስጡ በፀጋ የተሞላ መሆኑን ተገነዘቡ። ከመሪት ጋር በመለማማት ለሳሙኤል አዳዲስ ልብሶችን ለመግዛት ወደአንድ የልብስ መሸጫ ሱቅ ጎራ አሉ። የመደብሩ ሀላፊና አብረውት ያሉት ሰዎች ለሳሚ ዘመናዊ ተለማሚ ልብሶችን መረጡለት። ከላይ እስከታች ሁሉም አዲስ ሆነና ጉዞ ወደ መቃብር ሆነ። ስለሞተው ሰው ክብር ብዙ ሰዎች ተሰብስበዋል። መሪትም ብዙና የታወቁ ሰዎች እንደሚመጡ በመገመት ስብከቱን በጥንቃቄ ነው ያዘጋጀው። ከዚያም በላይ በሠረገላው ውስጥ የተደረገው ፀሎት አዲስ ሰው አድርጎታል። አሮጌ የአገልግሎት ሁኔታውንና አስተሳሰቡን ለውጦታል። የሚያውቋት አድማጮቹን የዚያ ዕለት ስብከቱና የሰውየው ሁለመና ተለውጦባቸዋል።

እንደቀድሞው በተለመደ የአነጋገር ስልቱና ቅደም ተከተሉ ሳይሆን ለማያት ተከፍተው መንፈስ ቅዱስ በርሱና በሰሚዎቹ ላይ የማፅናናት በረከቱን ባፈሰሰበት የተለየ አገልግሎት ድርሻውን ከጨረሰ በኋላ እነዚያም ሁለት ሰዎች በየተራቸው በነበራቸው አገልግሎት እንዲሁ ያ መለኮትዊ ኃይል በሰልጣን እንዲናገሩና በሁለመናቸው የእግዚአብሔርን በዚያ መገኘት የሚገልፅ ድርሻቸውን አበረከቱ።

ሕዝቡም በተናጋሪዎቹ መልዕክት ተነጥቀው በተመስጦ ሰምተውት የማያውቁትን መለኮታዊ ንግግርና በረከት በመለማታቸው ሁኔታው ሁሉ ከሀዘን ወደ ደስታ ተለወጠ። ለዚህ ለውጥ ምክንያት የሆነው ሳሙኤል ምንም ቃል አልተነፈሰም። ባለበት ሥፍራ በርጋታ ተቀምጧል። በሀሳቡ ወደ ለማያዊ ውድማ ዘልቆ ሔዷል ወደ እግዚአብሔር መንግሰት በመላዕክት አጀብ ለስገባችው ለለዚህ ሰው ነፍስና ለለሌሎችም እልፍ አእላፍ እድለኞች ያስባል። በዛው አንፃር እንደ እንሰሳ እየተራረዱ ያለቀብር አጥንታቸው ተበታትኖ የሚቀሩትን ወገኖቹን አስታወሰ። በዚያ ጫካ ውስት ለሚኖሩት ነበር ለሰሚመልኩት እንኳንስ በሞታቸው በሕይወታቸው የሚያፅናና ቃል ስላልተነገራቸው ወንጌልን ሳላለሙ ወገኖቹ ቀና በመጀመሪያ ወንጌል መስማትና ጌታን ማወቅ አለባቸው። ከዚያ በኋላ ኑሯቸውም ሞታቸውም ያምራል ሲል አሰበ።

ከቀብሩ ስነስርአት ፍፃሜ በኋላ አንግዳ ነገር ተፈጠረ። ማንም ሳይጋብዛቸው ሰዎች እየተግለተሉ ወደአገለገሉት ለዎች ማለትም እስክሬኑ ወዳረፈበት ሥፍራ መጡ። ለሞተው ለማልቀስ አልነበረም። ከሞተ ሥራቸው እየተናዘዙ ነፃ ለመውጣት ነበር። በዚያ ስፍራ ታላቅ የእግዚአብሔር ኃይል ስለነበር ልቦች ሁሉ ያላንግግር መልስ የሚስጡበት ቦታ ሆነ። በጌታ ያሉት በረከትን፣ ያለጌታ የነበሩት ደግሞ ሕይወትን አገኙ።

# ሳሚ ኮሌጅ ገባ

ከቀብሩ በኋላ ስቲቨን መሪት ከሳሙኤል ጋር ወደ ቢሮው ተመለስ። በመንገዳቸው ላይ የምርመራ ያህል ብዙ ብዙ ጥያቂዎች ተራ በተራ በመጠየቅ ሳሚ የልቡን መናገርና ማውጣት ጀመረ። መሪት ለመመለስ በታገለ መጠን ከአስተማሪነት ይልቅ ተማሪ በመሆን ከሳሙኤል ልምድ ብዙ ተማረ። ወደመንፈሳዊ ኮሌጅ ገብቶም እንዲማር ተስማሙ። ወዲያውኑ ለቴይለር ዩንቨርሲቲ ፕሬዜዳንት ደብዳቤ ተረቀቀ። ገና ከማዕድን ጉድጓድ የወጣ ያልተሰራ እንቁ ልኬላችኋለሁ ቀርፃችሁና አስተካክላችሁ ለዓለም እንዲያበራ እርዱት» በማለት መሪት ታላቅ አደራ ያላበትን የመሸኛ ደብዳቤ ካጠናቀቀ በኋላ ጉዞ ወደ ቤት ሆነ።

በማግስቱ ለንበት ነበርና አብረው ወደ ቤተክርቲያን ስመሄድ ተስማሙ። «የሰንበት ት/ቤቱ የበላይ ተቆጣጣሪ ስለሆንኩ ምናልባት ንግግር እንድታደርግ እጋብዝህ የሆናል» ሲል ሳሚን ዳርዳር አለው። «ለንበት ት/ቤት ተገኝቼም አገልግዬም ባላውቅም እንኳ እሺ ይሁን» በማለት ተስማማ።

ስዓቱ ደርሶ የሰንበት ተማሪዎቹ አዳራሹን ከሞሉ በኋላ ስቲቨን መሪት በፈገግታ ሳሙኤልን ሞሪስን ማለተዋወቅ ጀመረ። «ከአፍሪካ ነው የመጣው ዛሬ ስለመንፈስ ቅዱስ ያስተምረናል።» ብሎ ላይጨርስ ከፍሉ በሳቅ ተናጋ። ሁኔታው ገና ሳይረጋጋ መሪት ከመድረክ ላይ ለሌላ አስችኳይ ጉዳይ ተጠረቶ ስሙኤልን በመድረኩ ላይ እንዳለ ትቶት ወጣ። ከጥቂት ቆይታ በኋላ ሁኔታውን ለማረጋጋት ሲመለስ ሳሙኤል በመናገሪያው ቦታ ላይ ቆሞ ይፀልያል። የመድረኩ አካባቢ በሙሉ በሚያለቅሱና በሚንስቀስቁ ወጣቶች ተሞልቶ አገኘው።

ሳሚ በፀጥታ መፀለዩን ቀጠለ። በተፈጥሮውም የተረጋጋና ዝመተኛ ከመሆኑም በላይ ሲፀልይም «ካባቱ ጋር» ነው የሚወያየው። እድማጮቹን የሚወስድበት ምርጥና ብርቅዬ ቃላትን



አይደረድርም። ለቆመበት ሥፍራ መንፈስ ቅዱስን ይጋብዛል። ጉባኤውን ከታላቁ ኃይል ጋር ያገናኛል። ስፍራውም በእግዚአብሔር ክብር ይሞላል።

ከስብሰባው በኋላ በዚያ የተገኙትን የሰንበት ትምሕርት ቤት ተማሪዎች «የሳሙኤል ሞሪስ ሚሽነሪ ኅብረተሰብ» ተብሎ ወዲያው የተሰየመ ድርጅት መሠረቱ። ሳሚን ወደኮሌጅ ለመላክ ያሚያስፈልጉ ልብሶች፣ መፃህፍት፣ ገንዘብና ልዩ ልዩ ስጦታዎችንም ሰበሰቡ።

ከዚህም ሁሉ በኋላ ሳሚና መሪት ወደመኖሪያቸው ተመለሱ። የመሪት ባለቤት በታላቅ ትህትናና አክብሮት ለተዘጋጀው ማዕድ እንዲያመሰግን ሳሚን ጠየቀችው። በምስጋና መንፈስ ተሞልቶ ልመናውን በሰማያዊ አባቱ ፊት ባፈሰሰ ጊዜ በዚያ የነበሩት ልቦች ሁሉ እንደሸማ ቀልጠው መፍሰስ ጀመሩ። በወግ አጥባቂነት ያደገችውና በስሜት የማትገፋፋው ወ/ሮ መሪት እንኳን ሳትቀር ፀጥ ማለት አልቻለችምና በዕንባዋ በሰበሰች። ከምስጋናው በኋላ ሳሚን በጉጉት እያየች «ይህንን ቤት እንደራስህ ቤት ቁጠረው ያለንን ሁሉ ካንተ ጋር ለመካፈል ፈቃደኞች ነን» በጌታ እንድነታችውንና ቤተሰባዊነታቸውን ገለጠችለት።

ይሁን እንጂ እንዲማር በተወሰነው መሠረት በሳምንቱ አጋማሽ ላይ ዝግጅቱን አጠናቆ አርብ ዕለት ኮሌጁ ወደሚገኝበት ከተማ በሚወስደው ባቡር ተሸኝቶ እልም አለ። ከመርከብ ሲወርድ እንደነበረው ጊዜ ባይደናገርበትም በመጠኑ ግራ መጋባቱ አልቀረም። ሊያነባቸው የማይችላቸው መጽሐፍት ልብሶችና የስጦታ እቃዎች በአንድነት ተባብረው የመንገደኛ ሻንጣውን ውበት ቢስጡትም እንኳ ልጁ ለተመልካች ጥቁር ድሀ ፈደል የመቁጠሪያ ጊዜው የተላለፈበት ባዶ ነገር መስሎ ይታይ ነበር።

ይህ ሁሉ ሆኖ ሳለ ይህ ወጣት በብዙ የእግዚአብሔር ሰዎች ሕይወት ታይቶ የማይታወቅ የተለየ ፀጋው እየተገለጠ መጣ። ታዲዎስ ሲ ሪድ የተባሉት የኮሌጁ ፕሬዘዳንት ምን አይነት ክፍል እንደሚፈልግ ሲጠይቁት «ማንም የማይፈልገው ክፍል ካለ ያንን ለኔ ስጡኝ» ያለውን እኚሁ ሰው ከብዙ ጊዜ በኋላ አስታውሰው ቢፅፉ አይኖቼ በእንባ ተሞሉ። ሰዎች ሁሉ የማይፈልጉትን ለመቀበል ለሌሎች ቅድሚያ እስጥ እንደሁ ራሴን ጠየቅሁ። በኮሌጁ በቆየሁባቸው ዓመታት ከሺህ የሚበልጡ ተማሪዎችን በመቀበል አስተናግጃለሁ። ብዙዎቹ ከታላላቅ ቤተሰብ የመጡ የተከበሩ ወንዶችና ሴቶች ክርስቲያኖች ናቸው። የተሻለውን ከመምረጥ በቀር ስለነርሱ የማስታውሰው ነገር የለም። «ማንም የማይፈልገው ክፍል

# ክፍል 3

## የተማሪዎች መሪ፤ መለኮታዊ ስልጠና የተሰጠው አገልጋይ

ሐዋርያው ጳውሎስ አገልግሎቱን ከሰዎች ሳይሆን ከእግዚአብሔር እንደተቀበለ ይገልፃል። ይህ እውነት ለሳሙኤል ሞሪስም ይሰራል።

ሳሚ ዩንቨርሲቲው ወደሚገኝበት ፋትወይን በደረሰ በመጀመሪያው ሰንበት የጥቁጥሮች ቤተክርቲያን በአካባቢው እንዳለ ካረጋገጠ በኋላ በማለዳ ተነሰቶ ማፈላለግ ጀመረ። ኮሎጁ ካለበት ራቅ ይል ስለነበር የደረሰው ዘግይቶ ነው። ሌሎች አገልግሎቶች ሁሉ ተጠናቀው ሰባኪው የዕለቱን የሰንበት መልዕክቱን ለማሰማት መድረኩን ሲይዝ ሳሙኤል ወደ አዳራሹ ገባ። በቀጥታም መናገሪያው ወደሚገኝበት መድረክ በማምራት ሰባኪው ጋ ደረሰ።

ሰባኪው ለስነሥርዓት ሰፋ ያለ ሥፍራ የሚሰጥ ሰው ነው። የሳሚም ድፍረት ትዕግስቱን አሟጦበታል። ሰባኪው በመድረኩ ላይ እያለ ወደመናገሪያው ያለምንም ፈቃድና ጥሪ መምጣቱ አንሶት ሳሚ ጠጋ ብሎ «ሳሙኤል ሞሪስ እባላለሁ የመጣሁት ከአፍሪካ ሲሆን ለጉባኤያችሁ መልዕክት አለኝ» በማለት ነገረው። አገልጋዩ በቀጥታ ሊከለክለው ፈለገ። ነገር ግን በሰላም የተሞላውንና የሚያበራ ፊቱን ልብ ብሎ ሲመለከት የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳው ሰው እንዳልሆነ አሰበ። ምንአልባት መልዕክት ይኖረው ይሆናል አለ። በመቀጠልም መደበኛ ሰባኪ ለለመሰለው የሚናገርበትን ክፍል አዘጋጅቶ እንደሆነ ጠየቀው። «አላዘጋጀውም ነገር ግን መልዕክት አለኝ» ሲል መለሰለት።

መድረኩ ለሳሙኤል ተፈቀደለት። አገልጋዩም ወደ መቀመጫው ሄዶ የሚሆነውን በማጮለቅ ለመመልከት ተዘጋጀ። ወዲያውኑ ጉባኤው በፀሎት መንፈስ ተወሰደ። እያለቀሰና እየጮኸም ለፀሎት ተንበረከከ። በመድረኩ ላይ ያለው ሳሚ ቃል አልተነፈሰም። ነገር ግን ዝም ብሎ ቆሞ ይፀልይ ነበር «ከአባቱ ጋር ይነጋገራል» በዕለቱ መድረኩን ለሳሚ ትቶ የተቀመጠው ያ አገልጋይ ስለዚያ ቀን በሌላ ጊዜ ሲናገር «የሚለውን ለመስማት ብፈልግም ለዚያ የሚሆን ጊዜ አልነበረኝም። ከአቅሜ በላይ የሆነ የፀሎት መንፈስ ወረደብኝ። እንደሌላው በቦታው እንደነበረው አድማጭ ሁሉ ማንም ሳይለኝ ተነስቼ ተንበረከኩ። ሳሚ ምን እንዳለ፤ እኔም ምን እንዳልኩ አላስታውስም። የማስታውሰው ነፍሴ በመንፈስ ቅዱስ እሳት ተያይዛ



ትነድ እንደነበር ነው። ሳሙኤልን ከአፍሪካ ከእስራቱ ፈትቶ ያመጣው ያ ታላቅ ብርሃን በዚያ ጉባኤ በነበሩት ወገኖቻችን ላይ ሁሉ ያበራ ነበር። ያም ጉባኤ የዚህ ዓይነት የመንፈስ ቅዱስ ባርኮት ሲገጥመው የመጀመሪያው ነው

ስብሰባው ከተወሰነለት ሰዓት ብዙ ዘግይቶ ተበተነ። ሰዎቹም ወደየቤታቸው በተለያየ መንገድ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመገናኘታቸው ህልውናው እየተሰማቸው ሄዱ። ሳሚ በዚያ ቦታ ለሰዎቹ አልተናገረም። የእያንዳንዱን ነፍስ ጥማት መንፈስ ቅዱስ እንዲያረካ ለእግዚአብሔር የምልጃና የእምነት ንግግር አደረገ። ለዚህ የዕምነት ፀሎት መልስ የሚሆን የእግዚአብሔር ሙላት በዚያ ፈሰሰ። ሁሉም በደስታ ተሞልተው ሄዱ።

በፊት ዋይን ገና አንድ ሳምንት ያደረገው ሳሙኤል ሞሪስ ከዚያች የሰንበት አገልግሎቱ በኋላ ሁሉም የሚያውቀው ሰው ሆነ። የአካባቢው ጋዜጦች ሁሉ በዚያ የጥቁሮች ቤተክርስቲያን በሳሙኤል ሞሪስ አገልግሎት የተነሳውን የመንፈስ ቅዱስ መነቃቃት <ሪቫይቫል> በመጀመሪያው ገፃቸው አወጡት። በቅርብና በሩቅ ያሉ መንፈሳውያን ፀሀፊያን ሁሉ ስለታየው አስደናቂ ሪቫይቫል በስፋት አተቱ። በፊት ዋይን ቴይለር ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የሚገኘውም አፍሪካዊ ወጣት በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ በጠቅላላ ከተማዋ ታወቀ።

ይሁን እንጂ በሌላ በኩል የሳሙኤል ትምህርት ትልቅ ችግር አስከትሏል። በማንኛውም ክፍል ውስጥ ገብቶ ለመማርና በኮሎጅ ደረጃ ተቀባይነት ከማግኘቱ በፊት የብዙ ዓመታት ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና እንደሚያስፈልገው ግልፅ ነው በዚህ ጊዜ የአስራ ስምንት ዓመት ወጣት ቢሆንም እንኳ እንደ ትንሽ ልጅ ከፊደል መቁጠር መጀመር ነበረበት። ለዚህ ችግር መፍትሄ ተደርጎ የተወሰደውም አርምጃ በግል ለረጅም ጊዜ ከትንሽ ወደ ትልቅ የሚያስተምረውና የሚያስጠናው የግል አስተማሪ መመደብ ነው። በተማሪዎች የአምልኮ ስብሰባ ላይ ዶ/ር ሪድ የሳሚን ችግር አስመልክተው ሊያስተምረው ፈቃደኛ የሚሆን ሰው እንደሚፈልጉ ተናገሩ። ምንም እንኳ ቀላል ሥራ ባይሆንም ፈቃደኞች አልታጡምና የራሳቸው የዶ/ር ሪድ ሴት ልጅና ወ/ሪት ሃሪት ስቲመን የተባለችው ወጣት ህላፊነቱንና ወጣቱን ተረከቡ። ሆኖም በየጊዜው ሌሎችም ተጨማሪ ወንዶችና ሴት ፍቃደኞች በማስተማር ይረዷቸው ነበር።

## ሳሚ ለውድቀት የተቃረበውን ዩኒቪርሲቲ አዳነ

ሳሙኤል ሞሪስ የተማረውን ስመያዝ የሚጣጣር ትጉህ ተማሪ ነው። የምትነገረውን ቃል፣ ሀሳብና መመሪያ ሊጠፋ በማይችል ሁኔታ በአእምሮ ስሌዳው ይመዘግባል። በተማራቸው ቃላት አጭርና ሀሳቡን በትክክል ሊገልጡስት የሚችሉ አረፍተ ነገሮችን ይስራል። ቀልድና ፌዝ አያውቅም። ክቡር የሆነ ባህሪ ነበረው። ከባዱን ሀላፊነት የተረከቡት ሚስ ስቲመንና ሚስሪድ ቀስ በቀስ ስስራቸው ሽልማት የሚሆን በረከት እየበዛላቸው ሲሄድ ሥራው እየቀስላቸው እየወደዱትም መጡ።

ነገር ግን ከሁሉም በላይ ሳሙኤል በትምሕርቱና በኑሮው የመንፈስ ቅዱስን የበላይነት ይረዳ ነበር። ከአስተማሪዎቹ ያላነስ ንግግር ከስማያዊ አስተማሪው ጋር ያደርግ ነበር። ለርሱ ምድራዊ መምህራን በአጠገቡ ተገኝተው የሚያስተምሩትን ያህል መለኮታዊው አስተማሪ በጉኑ የመገኘት ነገር እውነትና እርግጠኛ ጉዳይ ነው። ብዙዎች ሳሙኤልን ስሚያትና ስማነጋገር ከርቀት መጥተዋል። ስተራ ወሬ ግን ጊዜ አይኖረውም። ከተለመደው የስላምታ ልውውጥ በኋላ የሚፈልገውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በመስጠት እንግዳው ጮክ ብሎ እንዲያነብለት ይጠይቀዋል ሳሚ በዚህ ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሱን ከዳር ዳር ወጥቶታል።

በዩንቨርሲቲው ውስጥ በጣም ተቃዋሚ የሆነ ኤቲስት ‹በእግዚአብሔር መኖር የማያምን› ሰው ነበር። ሰዎች የሚያምኑት ነገር እርሱን አያረካውም። በሚያምንበት ነገር በመከራከር የተካነ ነው። አማኝ ተማሪዎችን አነፍንፎ ለክርክር ይጋብዛቸዋል። አንተማመን ይላቸዋል። አሳምኑኝ ወይ ላሳምናችሁ በማለት መንገዳቸውን ላይ ይጋረጣል። ከሳሚ ጋር በቀላሉ መገናኘትም መወያየትም አይቻልም። ብዙውን ጊዜ በክፍሉ ውስጥ ስለሚፀልይ ማንም እንዲያቋርጥ ሊያደርገው አይችልም። ይሁን እንጂ ይህ የማያምን ሰው ከተማሪዎቹ አንዱን በማግባባት ወደ ሳሙኤል ክፍል እንዲወስደውና እንዲያስተዋውቀው አደረገ። ለክርክር ተዘጋጅቶ ጥያቄዎቹንና መልሶቹን ቅደም ተከተል አስይዞ በቀላሉ ድል እንደሚቀዳጅና ለዘላለም አፉን እንደሚያሲዘው ተማምኗል። ሳሚም ስጎብኚዎቹ እንደሚያደርገው መጽሐፍ ቅዱሱን ከፍቶ አንድ ምዕራፍ እንዲያነብለት ስጠው። ያም የማያምን ሰው መጽሐፍ ቅዱሱን ጠረጴዛ ላይ በመወርወር እንዲህ አለ «ያንን መጽሐፍ ከእንግዲህ አላነበውም ስለፍቅር፣ ስለጦርነትና ስለጎዛዎች ያወራል እኔ ግን ከውለጡ አንድም የማምናት ቃል የለችኝም።»



ሳሚ ከዚህ በፊት ከኤቲስት ጋር ተነጋግሮ አያውቅም። የአፍሪካ አረማውያን እንኳ ምንም ይሁን ምን አንድ መለኮታዊ ኃይል እንዳለ ያምናሉ። ሳሚም ይህንን ሰው ትኩር ብሎ እየተመለከተ ተነስቶ ወዳጠገቡ በመሄድ «ውድ ወንድሜ ዛሬ አባትህ ይናገርሃል አንተ ግን አላመንከበትም። እግዚአብሔር አባትህ ነው፣ ክርስቶስ ወንድምህነው፣ መንፈስቅዱስም ብርሃንህ» እጆቹንም በጎብኚው ትከሻ ላይ በማድረግ «ተንበርከክ እፀልይልሀስሁ» የእግዚአብሔር መንፈስ ለዚህ ነፍስ የሚሆነውን ነገር እንዲያስተላልፍ ረዳው። ያ ሰው ለጊዜው በእንቢተኝነት ከዚያች ክፍል ቢወጣም ከተወሰኑ ወራት በኋላ ተስወጠ። ታላቅ የፀሎት ሰውም ሆነ። በመጨረሻም አንድ ወቅት አሽሟጣጭ የነበረው ሰው ራሱን የቻለ የቤተክርስቲያን መሪ ሆነ።

ያ ዘመን የታመኑና ጌታን ስይተው ያወቁ ክርስቲያኖች የነበሩበትን ያህል እንዲሁ ደግሞ እያደገ በመጣው ዘመናዊነት ባስከተለውም ምኞት በተጨማሪም በዳርዊን የኢቮሊዩሽን ፍልስፍና ወደ ቤተክርስቲያን መግባት የተነሳ ብዙዎች ከእምነታቸው የተንሸራተቱበት በቤተክርቲያንም ካሉት ውስጥ የስም ክርስቲያኖች የሞሉበት ወቅት ነበር።

ቀደም ሲል የሜቶዲስት ቤተክርስቲያን መሪ እንደነበሩት ጆን ዊስሌይ ጥልቀት ያለው የእግዚአብሔር ቃል ትምህርትና የመንፈስ ቅዱስ የማንፃት ኃይል እየደበዘዘ በመምጣት በብዙዎች ሕይወት መንፈስ ቅዱስ የማይሰራበት ወቅት ነበር። የወንጌል ሥራ የኃይል ምንጭ የሆነው ይህ የእግዚአብሔር መንፈስ ሙላት ከብዙ አገልጋዮች ሕይወት እየሟሸሸ የመጣበት ጊዜ በመሆኑ ይህ እውነት በመሆኑ በቴይለር ዩኒቨርሲቲም ተንፀባርቋል።

የሳሙኤል ሞሪስ አገልግሎት ይህን እሳቱን ያጠፋ ዩኒቨርሲቲ ከፕሬዚዳንቱ እስከ አዲስ ገቢው ተማሪ አቀጣጠለው። የእግዚአብሔርም ፀጋ ሁሉን ወደሕይወቱ መለሰው። ት/ቤቱ በአጠቃላይ ከፍ ወዳለ ሕይወት ከመምጣታቸውም የተነሳ ደህንነትን ያገኙ ከመባል አልፈው ሌሎችን ሊያድኑ በሚችሉበት መንፈሳዊ ብርታት ስመገኘት በቁ።

የእግዚአብሔር መንፈስ ሰማያዊ በረከት ብቻ ሳይሆን ምድራዊም ቀጥሎ የሚመጣ መሆኑም በቴይለር ዩኒቨርሲቲ የሆነውን በመመልከት ስመረዳት እንችላለን። ኮሌጁ ስመውደቅ በሚንገዳገድበት የመጨረሻ የመፍገምገም ትግል በሚያደርግበት ወቅት በሳሙኢል ሞሪስ አገልግሎት ነፍሳት ተነቃቁ። የብዙዎች ተማሪዎችና ሠራተኞች መንፈሳዊ ሕይወት ከተዳፈነ እሳትነት

ወደሚንተገተግ የስደድ እሳትነት ተስወጠ። ይህ መንፈሳዊ በረከት የኮሌጁን ቁሳዊ ፍላጎት በሚያስገርም አኳኋን እስከማሟላት ተሸጋግሯል። የኮሌጁ ማገገም ራሱን በመቻል አላበቃም። ስለዚህ በሳሙኤል ሞሪስ ርዳታ ማስባሰቢያ ድርጅት ስም ሌላ ሰፋ ያለ መሬት ለመግዛት ለስታሰበ ለዚሁም የሚሆነው አስፈላጊ ገንዘብ በአጭር ጊዜ ተሠበሰበ። ሳሙኤል ሞሪስ ቴይለር ዩኒቨርሲቲን ከምድረበዳ አውጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር የመራ የኮሌጁ ሙሴ ነው ማለት ይቻላል። አዎ ሁሉም ነገር ተሳክቶ ውብ የሆነው አዲስ ቦታ ተገዛ።

## የመጨረሻ ጉዞ

ሳሙኤል ሞሪስ ተፈጥሮን የሚያደንቅና በእግዚአብሔርም የእጅ ሥራ የሚደነቅ ሰው ነበር። ይህ ከአፍሪካ ደን ውስጥ ያደገ ወጣት በትርፍ ጊዜው በአካባቢው ወደሚገኙ የአሜሪካን ጫካዎች መሄድና በውስጣቸውም በመንዝ የእፅዋቱን ሽታ የአእዋፋትን ዝማሬ በመስማት ጥሩ ጊዜ ያሳልፍ ነበር።

በሌላም በኩል በሩቅና በቅርብ በሚደረጉ መንፈሳዊ ስብሰባዎች ሳሙኤል የማይቀርር እንግዳ ነው። በተለይም ከባድ ክረምት በታየበት በ1892–93 ‹እ. ኤ. አ.› መንፈሳዊ ስብሰባዎችን በመካፈል ያስዕረፍት ያሳለፈበት ወቅት ነበር።

በዚሁ ዓመት በጥር ወር ከቅዝቃዜ የተነሳ ከባድ ጉንፋን ያዘው። ሕመሙ እየባሰበት ቢመጣም ምንም እንዳልሆነ ያህል ለማንም ሳይገልፅ ቆየ። ያስማቋረጥ ትምሕርቱን ለመከታተል ቢሞክርም ውስጥ ውስጡን እየጎዳው ከመጣው ብርድ የተቀላቀለበት የጉንፋን ህመሙ የተነሳ አቅሙ እየደከመ መጣ ምንም ሲደብቀው ባልቻለ ጊዜ ወደ ሆስፒታል ተወሰደ። ተኝቶ በሚታከምበት በዮሴፍ ሆስፒታል ያገለገላቸውና የሚወዱት ሁሉ ከመጎብኘትና ፍቅራቸውን ከመግለፅ አላቋረጡም።

ሳሚ በመጀመሪያ ለስህመሙ ብዙም የተረዳው ነገር አልነበረውም። ኋላ ግን እየተረዳ መጥቶ ሲጎበኙት ለሄዱ የክፍል ጓደኞቹ በጣም ደስ ብሎኛል። መላዕክትን አይቻቸዋለሁ አሁን በቅርብ ጊዜ ወደኔ መጥተው ይወስዱኛል ወደኔ የመጣው ያ ታላቅ ብርሃን በሕይወቴ አላማ ነበረው። ያዳነኝ ለአላማው ነው። አሁን ያንን አላማውን በሕይወቴ ፈፅሟል። በዚህችም ምድር ያለኝ ሥራ ተጠናቋል» በማለት በቅርብ ወደ አባቱ እንደሚሄድ ይናገር ጀመር።

ዶ/ር ሪድ ሳሚ ወደ አፍሪካ ተመልሶ ሲሰራው ለላስው የወንጌል አገልግሎት ጠይቀውት «አዎ ያ ሥራ የኔ ሥራ አይደለም።



የክርስቶስ ሥራ ነው። እርሱ ደግሞ የራሱን ሠራተኞች ይመርጣል። በሌሎች ያሰረዋል» የሚከታተሉት ሀኪም የዶ/ር ስቲመን መኖሪያ ከሆስፒታሉ ፊት ለፊት ነው ግንቦት 12 ረፋድ ላይ የግቢያቸው የአትክልት ቦታ እየበጃጁ ሳሉ የሚጣራ ድምፅ ሰሙ ብዙ አይድከሙ ዶ/ር ስቲመን» ቀና ብለው ቢመለከቱ ሳሚ ካለበት የሆስፒታል ክፍል በመስኮት የመጣ ድምፅ ነበር። ሁለቱም በፈገግታ እጆቻቸውን በማወዛወዝ ሰላምታ ከተሰጣጡ በኋላ ሳሚም ወደ ወንበሩ ተመለሰ። ዶክተሩም ተግባራቸውን ቀጠሉ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሲስተሩ ወደ ዶክተሩ መጥታ ሳሚ እንደ ደከመ አስታወቀች። ዶ/ር ስቲመን ወደ ሳሚ ክፍል ተፋጠኑ። ያ ወጣት አፍሪካዊ ግን በሰላም በወንበሩ ላይ እንደተቀመጠ ወዳላቱ ሄዷል። ከነዚያ ወደኔ ይመጣሉ ካላቸው መላዕክት ጋር ተደባልቋል።

## የብዙዎች ጥያቄ

የቴይለር ዩኒቨርሲቲ ያለበት ቦታ እየጠበበው ከመምጣቱም የተነሳ በተገዛው አዲስ ቦታ ላይ የመሠረት ድንጋይ ለማቆም እየተዘጋጀ ነው። በዚህም የመሠረት መጣል በዓል ላይ ሳሙኤል በመዝሙር እንዲያገለግልና ንግግርም እንዲያደርግ ታቅዷል። የታወቁ መንፈሳውያን ሰዎችም የሚገኙበት ስለሆነ ከተዘረጋው ሰፊ ፕሮግራም መረዳት ይቻላል ይህ በዚህ እንዳለ የሳሙኤል ሞሪስ ከዚህ ዓለም ማለፍ መላውን ተሳታፊ ኅብረተሰብ በጥልቅ ሀዘንና ድንጋጤ መታው። ብዙ ሊያገለል የሚችለው ይህ ወጣት በመቀጠፉ ብዙዎች በእግዚአብሔር ላይ እስከማጉረምረምና ግራ እስከመጋባት ደረሱ። ከዚህም በላይ የራሱ የሳሙኤል እምነት እንደ ደመና ተበታትኖ ቀረ በማለት ፍፃሜው አሳዘናቸው።

የሳሙኤል ሞሪስ አስከሬን የቀብር ስንስርዓቱ እስከሚደርስ በኮሌጁ የተማሪዎች የአምልኮ ክፍል ውስጥ ቆየ። ሰዓቱም እንደደረሰ ሳጥኑን የተሸከሙት ተማሪዎች ሳሚ አባል ወደነበረበት ቤተክርቲያን አመሩ። በመንገድ ላይ በመቶዎች የሚቆጠሩ ቆመዋል እንዲሁም ሌሎች ብዙዎች መቆሚያ ቦታ አንኳ በማጣትና ወደ ቤተክርቲያኑ መግባት ባለመቻል ዙሪያውን ከበዋል።

ከቤተክርቲያኑ ሥርዓት በኋላ ከዚያ በፊት ታይቶ በማይታወቅ እጅግ ብዙ ሕዝብ በተገኘበት የመጨረሻው ግብዐተ–መሬት ተፈፀመ። ኋላም በቴይለር ዩኒቨርሲቲ የመጨረሻ ዓመት ተማሪዎች በተሰራው ሀውልት ላይ እንዲህ የሚል ፅሁፍ ተቀረፀበት።

«ሳሙኤል ሞሪስ 1872–1893

ልዑል ካቡ

የምዕራብ አፍሪካ ተወላጅ

. . . . . . . . . . .

ባለሚስጥራዊ ኃይል ዝነኛ ክርስቲያን

የእምነት ሐዋርያ

በመንፈስ የተሞላና አርያነት ያለው»

ሀዘኑ ገለል እያለ ሲሄድ የሳሙኤል ሞሪስ እውነተኛ ሕይወትና አገልግሎት ምንነት በብዙዎቹ አእምሮ ወደንጋት መጣ፥ አስተማሪዎቹ ተማሪዎቹና ጓደኞቹ የእግዚአብሔር ሀሳብ ከነርሱ እንደሚበልጥና ለአላማውም በጎ እንዳደረገ እየተረዱ መጡ። ዶ/ር ሪድ ኋላ ሲፅፉ እንዲህ ብለው ነበር «ሳሙኤል ሞሪስ ለቴይለር ዩኒቨርሲቲ እግዚአብሔር በመለኮታዊ አሠራሩ የላከው መልከተኛ ነበር። ወደዚህ አመጣጡ የራሱን ሕዝብ ለማገልገል ለመዘጋጀትና ለመታጠቅ። ነበር ነገር ግን እውነተኛ አመጣጡ ቴይለር ዩኒቨርሲቲን ለመላው ዓለም አገልግሎት ለማዘጋጀት ሆኗል። ኮሌጁ አለም አቀፍ ራዕይ እንዲኖረው አነሳስቷል። ከሀገራዊም ወደ አለም አቀፋዊ አገልግሎት ተሸጋግሯል።

በርግጥ ሳሙኤል ሞሪስ በሕይወት ኖሮ ወደ አፍሪካ ቢመለስ አንድ ሰው ነውና በአንድ አካባቢ ብቻ የሚወሰን አገልጋይ ይሆን ነበር። አፍሪካን በወንጌል በማዳረስ ረገድ ታላቅ ጅማሬ ጥሎ አልፍዋል። ሳሚ ከሞተ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በተደረገው ፀሎት አንድ ጎልማሳ ተነስቶ «በሳሚ ቦታ ወደ አፍሪካ መሄድ እንዳለብኝ ይሰማኛል። የርሱም ሸክም በኔ ላይ ወድቋል። ሥራው ብቻ ሳይሆን የእምነቱም መጎናፀፊያ እንዲወደቅብኝ አፀልያለሁ።» ብሎ ከመቀመጡ ሌሎች ሁለት ፍቃደኞችም በተመሳሳይ አቋም ከዚሁ ሰው ጋር ተባበሩ። እነዚህን በመከተል ሌሎችም እጅግ ብዙዎች ወንጌልን ወደአፍሪካ ለማዳረስ የነዚህን ፈለግ ተከተሉ።

አዎን ሳሙኤል ሞሪስ በሞቱ ብዙዎችን ወደ አፍሪካና ወደ ሌላውም አለም ለወንጌል ሥራ አነሳሳ። ወደ ሀገሩ በመመለስ አንድን አካባቢ ብቻ ከመጥቀም ይልቅ ለአለም ሁሉ ሊጠቅም በሚችልበት መንገድ እግዚአብሔር ሀሳቡን ፈፀመበት።



ከዚህ ሁሉ በላይ በነጮችና በጥቁሮች መሀል ክርስቲያናዊ ወንድማማችነትንና መቀባበልን ለማምጣት ረድቷል። ኋላም አስከሬኑ ነጮቹና ጥኩሮች ወደ ሚቀበሩበት የመቃብር ቦታ ተዛውሮ በክብር አረፈ። በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ጎብኚዎች መቃብሩን ለማየት ወደዚህ ቦታ ጎርፈዋል።

## ሥራው ከሳሚ ጋር አልሞተም።

ሳሙኤል ሞሪስ ቢያንከቀላፋም እንኳ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የቆመባቸው መድረኮች ሁሉ ያለማረጥ በማፍራት ለብዙ አመታት ቀጥለዋል። ለብዙ ዓመታት ያላቋረጠ መንፈሳዊ ለውጥ ከተካሄዱባቸው አንዱ ቴይለር ዩንቨርሲቲ ነው። ሳሚ እንዳረፈ ሶስት ፍቃደኞች የርሱን ሸክም ለመወጣት ወደ አፍሪካ መጡ። ቀጥሎም በዛው ዓመት ሰባት ተከተሉ። ያለማቋረጥ ክርስቲያን መምህራንና ሰባኪዎች በሳሚ ሕይወት በነበረው የተቀጣጠለ ሕይወት ወደዚሁ የዓለም ክፍል ያለማቋረጥ ጎርፈዋል። መስዋዕትነት እስከመከፈልም የደረሱና በአፍሪካ ምድር የተቀበሩ እንደ አሲቨርየር ከዚሁ ኮሌጅ የተገኙ ናቸው። ከዚህም በላይ የቴይለር ዩንቨርሲቲ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት በአፍሪካ እስከመከፈት ደርሷል። ይህ ሁሉ ቴይለር ዩኒቨርስቲ ካደረገው ጥቂት ሲሆን ወደ ዓለም ሁሉ የሚሄዱ ሚሲዮናውያንንና ክርስቲያን አስተማሪዎችን ማሰልጠኛ ማዕከል በመሆን ካንድ ትውልድ በላይ ለሆነ ዘመን በተሳካ ሁኔታ አገልግሎቱን ተወጥቷል።

በሁሉም አገልግሎት ሳሚ ጊዜያዊ ለውጥ ሳይሆን ዘላቂና በሰዎች ሕይወት ፍሬ እየፈራ የሚዘልቅ ለውጥን አስከትሏል። ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ ያ ባለመርከብ ካፕቴን ወደ ኒውዮርክ በመምጣት ስቲቨን መሪትን አፈላልጎ ለማግኘት ቻለ። በቀጥታ የጠየቃቸው ሳሙኤልን ነበር። ነገር ግን ሳሙኤል ሞሪስ ገና በሀያ አንድ ዓመቱ ወደ ክብር ሄዷል ባለው ጊዜ ከድንጋጤው የተነሳ ለተወሰኑ ደቂቃዎች መናገር አልቻለም። ኋላም ብዙዎቹ የቀድሞዎቹ ባህረኞች ከርሱ ጋር እንዳሉና አሁንም የጀግናውን አገልጋያቸውን ወሬ ለመስማት በጉጉት እንደሚጠብቁት አጫወተው እንደ አንድ ቤተሰብ እንደሚተያዩና የሕይወት ለውጡም እንደዘለቀላቸው በደስታ የተሞሉና የህይወትንም ጣዕም የተረዱ መሆናቸውን ነገረው።

የስቲቨን መሪት መላ አገልግሎትና ሕይወትም እንዲሁ ሙሉ ለሙሉ በመለወጡ እስከ ዕለተ ሞቱ ሌላ ሰው ሆኖ ነውሩጫውን የጨረሰው። ከሳሚ ጋር እንደተለያዩ ስቲቨን መሪት በቀጥታ ወደ እብዶች ሆስፒታል ነበር የሄደው። በዚያም ለብዙዎች ፀለየ ጤነኛም ሆኑ። በየሆስፒታሉ እየዞረ ለበሽተኞች መፀለይን

ቀጠለ እግዚአብሔርም ባገልግሎቱ ታምር ይሠራ ነበር። የእረኝነት አገልግሎቱን ከማቆሙ በፊት እንኳ አስር ሽህ ያህል ሰዎች ወደ ጌታ ለማምጣት ችሏል።

ላሚ ያገለገለው ያ የስንበት ት/ቤትም በዚያው ዓመት ከሺህ የሚበልጡት አዳዲስ ነፍሳትን ወደ ቤ/ክ አምጥቷል። ያቋቋሙትም የሳሙኤል ሞሪስ መርጃ ድርጅት ዘላቂ ውጤት አስገኝቷል። ችግረኞችን የሚረዳ ታላቅ ድርጅት ወጥቶታል።

በመጀመሪያው ሰንበት ያገለገላቸው የጥቁሮች ቤ/ክ አባላትም በዛው ዓመት በተጨመሩት ብዙ አባላት የቀድሞው በታ ስለጠበባቸው አዲስ ቤ/ክ ለመገንባት በቅተዋል።

በቴይለር ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በዶ/ር ሪድ የተመሰረተውም የሳሙኤል ሞሪስ የእምነት ድርጅት እየሰፋና ታላቅ ውጤት እያመጣ ሄዷል። ከሦስት ዓመት በኋላ እንደ ሳሙኤል መማሪያ የሌላቸውን አንድ መቶ ተማሪዎች አስልጥኖና አዘጋጅቶ ለወንጌል ሥራ አሰማርቷል። እያደር ይህን ድርጅት ለመርዳት ከሀገር ውስጥ አልፎ ከውጭ ድረስ እርዳታ በሰፊው ይደርሰው ጀመር። ከተመሠረተ ከአርባ አመት በኋላ እንኳ የሚጎርፈው እርዳታ ቀላል አልነበረም።

ቴይለር ዩኒቨርሲቲ ያሰራውን የአዲሱን ኮሌጅ ታላቅ አዳራሽ በሳሙኤል ሞሪስ ስም ሰየመው። የፎርትወይን ከተማ ነዋሪዎች በጠየቁት መሠረት አዲስ ይሠሩ የነበሩት ቤቶች የሳሙኤል ሞሪስ መንደር እንዲባል መንግስት በመፍቀዱ በነዚህና በሌሎችም ነገሮች ሁሉ ይህ ወጣት በግለሰቦች በድርጅቶችና በመላው ከተማ ሳይቀር የማይረሳ ትዝታ ጥሎ አለፈ።